# አዲስ ዘመን

አንድ

ዓርብ

82ኛ ዓመት ቁጥር 111 ታኅሣሥ 21 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!


# “ሰላም ከሰፈነ የበለጸገች ኢትዮጵያን ማየት ሩቅ አይሆንም “

- አቶ አባተ ኪሾ

የቀድሞ የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ርዕሰ መስተዳድር



ፎቶ፡ ከፋያስ

ዋቅሹም ፍቃዱ

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ የነበረው የሰላም እጦት ችግር በዘላቂነት ከተፈታ የበለጸገች ኢትዮጵያን ማየት ሩቅ እንደማይሆን የቀድሞው የደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል ፕሬዚዳንት አቶ አባተ ኪሾ ገለጹ። ሁሉም ተበዳይና ይቅር ባይ ሆኖ ከቀረበ በኢትዮጵያ ምድር የማይፈታ ችግር አለመኖሩን የሰላም ስምምነቱ ማሳያ መሆኑንም ጠቁመዋል።

አቶ አባተ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፣ በሕወሓትና በፌዴራል መንግሥቱ መካከል የተደረገው የሰላም ስምምነት ሁለቱ ወገኖች ለሰላም ያላቸውን ፍላጎት ያሳየ ነው ብለዋል። በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈጉባኤ አቶ ታገሰ ጫፎ የተመራው የልዑካን ቡድኑ በመቀሌ መሔዳቸው የሰላም ስምምነቱ በትክክል መሬት ላይ መውረዱን ያሳያል ነው ያሉት።

የአገሪቱን ሰላም የተሟላ ለማድረግ በተለይም በኦሮሚያ ክልል ያለው የጸጥታ ችግር የሚፈታበት ሁኔታ ላይ መስራት ያስፈልጋል ያሉት አቶ አባተ፤ በሰሜኑ የተደረገው ጦርነት መጠነ ሰፊ ከመሆኑ የተነሳ በሰው ሕይወት፣ በንብረትና በአገር ገጽታ ያደረሰው ጉዳት በቀላሉ የሚገመት አይደለም ብለዋል። ይህንን የጸጥታ ችግር በአጭር ጊዜ ውስጥ እልባት መስጠት ከተቻለ በሌሎች አካባቢዎች ያሉትን የፀጥታ ችግሮች መፍታት ጊዜ ይወስዳል የሚል እምነት እንደሌላቸው ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ ግጭትን በራሷ አቅም የመፍታት ረጅም ልምድ ያላት አገር እንደመሆኗ መጠን ከዚህ በኋላ ማናቸውም ግጭቶች ያለ ሦስተኛ ወገን በአገር ሽማግሌዎች እና በሐይማኖት አባቶች በኩል በውስጥ አቅም መፈታት አለባቸው ያሉት አቶ አባተ፤ ለዚህም የፌዴራል መንግሥት የልዑካን ቡድን ወደ መቀሌ ያደረጉት ጉዞ የውስጥ ችግር በውስጥ አቅም ለመፍታት ከሚደረገው ጥረት አንዱ ማሳያ ይሆናል ብለዋል።

“ሰላም ከሰፈነ ... ወደ ገጽ 12 ዞሯል

## የመማርያ መጽሐፍት በበቂ ሁኔታ ባለመሟላቱ መቸገራቸውን መምህራንና ተማሪዎች ተናገሩ

ሙሳ ሙሐመድ

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ በአዲሱ ፍኖተ ካርታ ትምህርት መስጠት ቢጀመርም መጽሐፍት ባለመሟላታቸው የመማር ማስተማር ሂደቱ ችግር እየገጠመው መሆኑን መምህራንና ተማሪዎች ተናገሩ።

በአዲስ አበባ የምኒልክ አጸደ ህጻናትና መጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር አቶ አሳዬ የኋላሸት እንደገለጹት፤ በአዲሱ የትምህርት ፍኖተ-ካርታ መሰረት የተዘጋጀው መጽሐፍ አልቀረበም፡፡ መጽሐፉ ሳይቀርብ ትምህርቱን እንደናስተምር መደረጉ ፈታኝ ነው፡፡

በአዲስ አበባ ትምህርት ቤቶች ባልተሟላ የትምህርት መርጃ መሳሪያ የሚሰጠው ትምህርት የትምህርት ዘመኑ አጋማሽ ላይ ተቃርቧል፡፡ ችግሩ የመማር ማስተማር ሥነ-ዘዴውን ቢቀይረውም ችግሩን አግዝፎታል ብለዋል፡፡

ለማስተማሪያነት እንዲውሉ የተሰጧቸው የጠቅላላ ሳይንስ፣ የሰውነት ማጎልመሻና አማርኛ መጽሐፍት ብቻ

የመማርያ መጽሐፍት... ወደ ገጽ 12 ዞሯል



## በትግራይ ክልል

### አስቸኳይ የሰብዓዊ ድጋፍ በስፋት እየቀረበ መሆኑንና መሰረታዊ አገልግሎቶችም መጀመራቸውን ኦባሳንጆ አረጋገጡ

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- የሰላም ስምምነቱን ተከትሎ በትግራይ ክልል አስቸኳይ የሰብዓዊ ድጋፍ በስፋት እየቀረበ መሆኑንና መሰረታዊ አገልግሎቶችም መጀመራቸውን በአፍሪካ ህብረት የአፍሪካ ቀንድ ልዩ መልእክተኛ አሊሴጉን ኦባሳንጆ ገለጹ።

የህብረቱ ልዩ መልእክተኛ አሊሴጉን ኦባሳንጆና የቀድሞ የኬንያ ፕሬዚዳንት ኡሁሩ ኬንያታ፤ በመንግሥትና ሕወሓት መካከል የተደረሰውን የሰላም ስምምነት ተከትሎ አፈፃፀሙን ለመመልከት በመቀሌ

በትግራይ ክልል... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ፡ አሸናፊ ጉደታ

ዶክተር ፍስሃጽዮን ገብረመድህን

## የስሁል ሽሬ ጠቅላላ ሆስፒታል ነጻ የህክምና አገልግሎት እየሰጠ ነው

አዲሱ ገረመው

ሽሬ፡- ጤና ሚኒስቴር ባስቀመጠው አቅጣጫ መሰረት ከሰላም ስምምነቱ ወዲህ የስሁል ሽሬ ጠቅላላ ሆስፒታል ለበርካታ ዜጎች ነጻ የህክምና አገልግሎት

የስሁል ሽሬ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር

ደርባ ሲሚንቶ DERBA CEMENT



በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72

ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና 0111 26 23 18

ይዘዙን

ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።

ነገን ዛሬ እንሥራ



ፀደይ ባንክ (አ.ማ)
TSEDEY BANK (S.C)

የሁሉም ባንክ
Bank for all !

የብዙዎችን ተስፋ ያለመለመ!

በፋይናንስ አቅርቦት በተግባር የተፈተነ እንዲሁም ሰፊና ጽኑ መሰረት ያለው ባንክ በአነስተኛ የፋይናንስ አገልግሎት ዘርፍ በአገለገለባቸው 25 ዓመታት አለም አቀፍ ዕውቅናዎችን ሲያገኝ የቆየው አማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም ወደ ፀደይ ባንክ ተሸጋግሮ የተሟላ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡

Tel: +251 115 58 12 70/011 551 73 48/011 558 99 98
P.O.Box: 9630
E-mail: mekonnenyelewemwessen@tsedeybank-sc.com
Web: www.tsedeybank.org.et
Addis Ababa, Ethiopia



eccs

የኢትዮጵያ የግንባታ ግብዓቶች አቅራቢ ኃ/የተ/የግል ኩባንያ
ETHIOPIAN CONSTRUCTION COMMODITIES SUPPLY PLC.

የአርማታ ብረት እና ሌሎች ብረታብረቶች አከፋፋይ



Mob. 0911 225057/ 0989 343434

አድራሻ፡ ከሜክሲኮ አደባባይ ወደ መርካቶ በሚወስደው መንገድ ከዲ-አፍሪክ ሆቴል ፊት ለፊት









«ለነዋሪዎች ቀልጣፋ አገልግሎት መስጠት በውብ ከተማ ግንባታው ቅድሚያ የተሰጠው ተግባር ነው»

- ከንቲባ አዳነች አቤቤ

ገጽ 3

# የጌዴኦ ባህላዊ መልከዓ ምድር በዩኔስኮ ሲመዘገብ ነው

**ዳግም ከበደ**

ጌዴኦ፡- የጌዴኦ ባህላዊ መልከዓ ምድርን በዓለም ቅርስ ቋሚ መዝገብ ለማስመዝገብ እየተደረገ ያለው ጥረት የመጨረሻ ደረጃ ላይ መድረሱን የኢትዮጵያ የቅርስ ባለሥልጣን አስታወቀ። የመስህብ ሀብቱ አስፈላጊውን ሰነድ አሟልቶ የ "ይመዝገብ" ይሁንታን ከተባበሩት መንግሥታት የትምህርት የሳይንስና የባህል ድርጅት ዩኔስኮ እየተጠባበቀ ነው።

የመገናኛ ብዙሃን አባላትን የመስህብ ስፍራውን በጎበኙበት ወቅት የኢትዮጵያ ቅርስ ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር ረዳት ፕሮፌሰር አበባው አያሌው እንደገለጹት፤ የጌዴኦ ባህላዊ መልከዓ ምድር ረጅም ዘመናትን ያስቆጠሩ የዞኑ ቅርስ ሀብቶችን በዓለም ቅርስነት ለማስመዝገብ፣ ለማስተዋወቅና የቱሪስት መዳረሻ ለማድረግ እየተሰራ ነው። በዩኔስኮ የዓለም ቅርስነት የማስመዝገብ ሂደቱ በባለሙያዎች የተሟላ ሰነድ ቀርቦ ከድርጅቱ አዎንታዊ ምላሽ ተገኝቷል። በቀጣዮቹ ወራትም በሚካሄደው ጉባኤ ላይ በጎ ምላሽ ይገኛል ተብሎ ይጠበቃል።

"የጌዴኦ ደን ሀብትና ባህላዊ መልከአ ምድር ለአፍሪካ ምሳሌ የሚሆን ነው" ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ በጌዴኦ ሰው ሲበዛ የደን ሀብት ይበልጥ ይጨምራል እንጂ እንደሌላው አካባቢ አይመናመንም። ለመልከዓ ምድሩ መጠበቅና የቱሪዝም መስህብነቱን ሳይለቅ መቆየት የማህበረሰቡ ቱባ ባህል ዋናውን ድርሻ ይወስዳል ብለዋል። ይህ እሴት ለሌሎች አካባቢዎች ምሳሌ የሚሆንና ለተፈጥሮ ሀብት የምንሰጠው ክብር እንዲጨምር የሚያደርግ መሆኑን ነው።

የሶስት ሺህ ዘመን ታሪክ ባለቤት የሆነችው ኢትዮጵያ የበርካታ ባህላዊ፣ ታሪካዊና ተፈጥሯዊ መስህቦች በትውልድ ቅብብሎሽ ዘመናትን ተሻግረው፣ በግማሽ ምእተ ዓመት ውስጥ ዘጠኝ የሚዳሰሱ እንዲሁም አራት የማይዳሰሱ በአጠቃላይ አስራ ሶስት ቅርሶቿን በዓለም አቀፍ ቅርስነት በማስመዝገብ ከአፍሪካ ቀዳሚ መሆኗንም የገልፃሉ፡፡ እነዚህ በዩኔስኮ የዓለም ቅርስነት የተመዘገቡት ቅርሶች ዛሬ ላይ ህያው ምስክሮ ከመሆንም ባሻገር በቱሪስት መስህብነት የውጭ ምንዛሬ በማስገኘት ኢኮኖሚውን እየደጎሙና አገርንም ለመላው ዓለም እያስተዋወቁ እንደሚገኙ ያስረዳሉ።

"በዩኔስኮ በዓለም አቀፍ ቅርስነት በጊዜያዊነት የተመዘገቡና በቋሚነት ለማስመዝገብ ባለፉት ዓመታት በርካታ ጥረቶች ሲደረጉ ቆይቷል" የሚሉት ረዳት ፕሮፌሰሩ፤ በመገናኛ ብዙሃን የተጎበኘው ለዓለም ማህበረሰብ ለማስተዋወቅ ሰፊ ዝግጅት እየተደረገበት የሚገኘው የጌዴኦ ባህላዊ መልከዓ ምድር ቅርስ ተጠቃሽ መሆኑን ያነሳሉ።

የቅርስ ጥበቃ ባለሥልጣን መስሪያ ቤት የጥናትና ምርምር ዳይሬክተር አቶ አንዱአለም የጌዴኦ ባህላዊ መልከዓ ምድር ቅርስ የምዝገባ ሂደት ነባራዊ ሁኔታ የተመለከተ ፅሁፍ ለመገናኛ ብዙሃን ባለሙያዎች ያቀረቡ ሲሆን ለዩኔስኮ የመጨረሻ የምዝገባ ሂደት ላይ የደረሰው "የጌዴኦ ባህላዊ መልከዓ ምድር" የእርሻና የደን ጥበቃ ሀገር በቀል እውቀት፣ ትክል ድንጋዮች፣ የዋሻ ውስጥ ስዕሎች፣ጥብቅ ደኖች እንደተካተቱበት ተናግረዋል።

የሜጋሊቲክ አርኪኦሎጂካል ስፍራዎች በብዛት እንደሚገኙ የገለጹት ረዳት ፕሮፌሰር አበባው፤ ለአብነትም ቱቱ ፈላ ሜጋሊቲክ፤ ጨልባቲቲ ሜጋሊቲክ፣ ሴዴ መርካቶ ሜሜጋሊቲክ ፣አዶላ ጋልማ ሮክ ጥበብ እንዲሁም የተቀደሱ ደኖች እና ሌሎችም በርካታ እምቅ ሀብቶች ይገኛሉ ብለዋል፡፡

በሚዳሰስ ቅርስነት ከዲላ እስከ ወግድ አምባ ያለው አካባቢም በጥምር ግብርና ሥርዓት፣ በመልካ ምድሩና በጥቅጥቅ ጥብቅ ደን የታደለ ነው። ይህ ባህላዊ ሀብት በዩኔስኮ በዓለም ቅርስነት ጊዜያዊ ምዝገባ ውስጥ እንዲካተት ከማድረጉም ባሻገር በቋሚነት ሊመዘገብ የመጨረሻውን ውጤት እየተጠባበቀ ይገኛልም ብለዋል።

ይህንን ሁሉ ሀብት አስተሳስሮ የያዘው መልከአምድርም በቅርቡ በሚካሄደው የተባበሩት መንግሥታት የባህል፣ የኪነጥበብ እና የትምህርት ድርጅት የሆነው ዩኔስኮ ስብሰባ ላይ በቋሚነት እንዲመዘገብ ሊወሰን እንደሚችል ነው የተናገሩት።

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት ባህላዊ መልከዓ ምድሩ ባሳለፍነው ዓመት ይመዘገባል ተብሎ ቢጠበቅም በሩሲያና ዩክሬን መካከል በተነሳው ጦርነት ጉባኤው ላልተወሰነ ጊዜ በመራዘሙ ሳይሳካ ቀርቷል።

# የደምና ቲሹ ባንክ

## -140 ሺህ ዩኒት ደም ሰብስቧል

## -ለአክሱም ከተማ 200 ዩኒት ደም ሰጥቷል

**ሄለን ወንድምነው**



አቶ ሀብታሙ ታዬ

አዲስ አበባ፡- በአምስት ወር ውስጥ 140 ሺህ ዩኒት ደም መሰብሰብ መቻሉን የኢትዮጵያ ደምና ቲሹ ባንክ አገልግሎት አስታወቀ፡፡ ከሰላም ስምምነቱ ወዲህ በአክሱም ከተማ ለሚገኙ ታካሚዎች የሚውል 200 ዩኒት ደም ሰጥቷል፡፡

የኢትዮጵያ የደምና ቲሹ ባንክ አገልግሎት ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ሀብታሙ ታዬ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በ2015 በመላው ኢትዮጵያ በዓመት 490 ሺህ ዩኒት ደም ለመሰብሰብ ታቅዷል፡፡ በአምስት ወራት ውስጥ 140 ሺህ ዩኒት ደም ተሰብስቧል።

አቶ ሀብታሙ እንዳሉት፤ በአምስት ወር ውስጥ 190 ሺህ ዩኒት ደም እንደሚሰበሰብ ታቅዶ ነበር፤ ይሁንና የደም ለጋሾች ተሳትፎ በተወሰኑ ወራት ዝቅተኛ በመሆኑ ከዕቅድ በታች አፈጻጸም እንዲመዘገብ ምክንያት ሆኗል።

ባለፈው የክረምት ወቅት ትምህርት ቤቶች ዝግ በመሆናቸው፤ ወቅቱ ቅዝቃዜ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ደካማ የደም ልገሳ አፈጻጸም የታየበት መሆኑንም አቶ ሀብታሙ አንስተዋል፡፡ ይሁን እንጂ ጥቅምት ወር 2015 ዓ.ም ከገባ አንስቶ በተለያዩ ዘመቻዎች አማካኝነት የደም ልገሳ እንቅስቃሴዎች መጠናከራቸውን ጠቀመዋል።

እንደክልል ያለውን የደም ልገሳ አፈጻጸም በተመለከተ የተወሰኑ ክልሎች ላይ ደካማ እንቅስቃሴ መኖሩን የተናገሩት አቶ ሀብታሙ፤ በአዲስ አበባ፣ በአማራና ኦሮሚያ ክልሎች የተሻለ አፈጻጸም እንዳለ ተናግረዋል።

በአንጻሩ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ አፋር፣ ጋምቤላ፣ ሲዳማ እንዲሁም ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ላይ ደግሞ የደም ልገሳ አፈጻጸሙ ዝቅተኛ ነው። የየክልሎቹ የደም ባንኮች የደም አሰባሰብ ልምዱ እንዲጠናከር የሚረዳ አቅጣጫ ተቀምጦ ከጥቅምት ወር ጀምሮ በስፋት እየተሰራ ይገኛል ብለዋል።

በየዓመቱ የደም ተጠቃሚዎች እየጨመሩ ቢመጡም በዚያው ልክ የደም ፍላጎቱም በከፍተኛ ሁኔታ መጨመሩን የገለጹት ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ፤ ከተጠቃሚዎች ፍላጎት ጋር አብሮ የሚያድግ የደም ልገሳ ባህል መኖር እንዳለበትም ጠቁመዋል።

እንደ አቶ ሀብታሙ ገለጻ፤ የአንድ አገር የደም አቅርቦትና ፍላጎት በበቂ ሁኔታ ተሟልቷል ተብሎ የሚታሰበው በመደበኛነት የደም ለጋሾች ሲኖሩ ነው፡፡ ይህም አጭር የመጠቀሚያ ጊዜ ያለውን ደም በየጊዜው በመለገስና በመተካት የድንገተኛ የነፍስ አድን ሕክምናዎችን ማገዝ ያስችላል።

አሁን ባለው የደም ፍላጎት መሰረት በመደበኛነት በየሦስት ወሩ ደም የሚለግሱ ግለሰቦችን ማግኘት ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ነው ብለዋል።

ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ እንዳስታወቁት፤ ደምና ቲሹ ባንኩ በዋናነት የደም ማሰባሰብ ስራውን ከበጎ ፍቃድ ደም ለጋሾች ጋር በትብብር በማከናወን የተሰበሰበውን ደም ጥራት የማስጠበቅ ስራ ያከናውናል።

ጥራቱን ጠብቆ እንዲቀመጥ የተደረገውን ደም ለሚያስፈልጋቸው ሰዎችና አገልግሎቱን ለሚሰጡ ተቋማት በማሰራጨት ኃላፊነቱን እየተወጣ ይገኛል ብለዋል። በአጠቃላይ በኢትዮጵያ 43 የደም ባንኮች እንዳሉ የገለጹት አቶ ሀብታሙ፤ ከዚህ ውስጥ ሶስቱ በትግራይ ክልል ውስጥ የሚገኙ መሆናቸውን ጠቁመዋል።

በሰሜን ኢትዮጵያ የነበረውን ግጭት ለማቆም ከተደረሰው የሰላም ስምምነት በኋላ አክሱም የሚገኘው የደም ባንክ ደም የመሰብሰብ ስራውን እስከሚጀምር ለታካሚዎች የሚሆን 200 ዩኒት ደም ተሰጥቷል ሲሉ አስታውቀዋል። በክልሉ የሚገኙ ሶስቱ የደም ባንኮች በፍጥነት ወደ ስራ እንዲገቡ የተለያዩ ግብዓቶች እየተሟሉላቸው እንደሚገኙም አቶ ሀብታሙ ገልጸዋል፡፡

የዓለም ጤና ድርጅት በአንድ አገር ከሚኖሩ ሕዝቦች መካከል ቢያንስ አንድ በመቶ የሚሆኑት ደም ለጋሽ መሆን እንዳለባቸው ምክረ ሃሳብ አስቀምጧል። በ2014 ዓ.ም በኢትዮጵያ 337 ሺሕ ዩኒት ደም ተሰብስቧል።

# ዞኑ የክልል ምስረታ ሕዝበ ውሳኔው በሰላም እንዲካሄድ ዝግጅት ማድረጉን ገለጸ

**መክሊት ወንድወሰን**



አቶ ካሳሁን አባይነህ

አዲስ አበባ፡- የጎፋ ዞን የክልል ምስረታ የሕዝበ ውሳኔው እንቅስቃሴ ሰላማዊ መሆኑንና ምርጫው በሰላም እንዲጠናቀቅም በትኩረት እየሰራ መሆኑን የጎፋ ዞን አስታወቀ።

የዞኑ የመንግሥት ጉዳችዮች ኮሚዩኒኬሽን ኃላፊ አቶ ካሳሁን አባይነህ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፣ ምርጫው በሰላማዊ ሁኔታ እንዲጠናቀቅ የምርጫ ካርድ ለሕዝቡ ከመሰጠቱ በፊት ለጸጥታ አካላት የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና ተሰቷል። በተጨማሪም ሕዝቡ ሰላሙን እንዲጠብቅ የማደራጀት ሥራም እየተሰራ ነው።

በዞኑ እና ወረዳዎቹ የሚገኙ የጸጥታ አስከባሪ ሚሊሻ፣ የፖሊስ ሠራዊት አባላትና የክልሉ ልዩ ሃይል የክልሉን ሰላምና ጸጥታ ለመጠበቅ ሙሉ ዝግጅት አድርገዋል ያሉት ኃላፊው፤ ምርጫው የተሳካ እንዲሆን ሕዝቡም ከጸጥታ አካላት ጋር በመተባበር የተለያየ ተሳትፎ እያደረገ መሆኑን አስታውቀዋል።

እንደ አቶ ካሳሁን ማብራሪያ፣ ከታህሳስ 11 ጀምሮ እየተካሄደ ባለው የክልል ምስረታ ሕዝበ ውሳኔ የመራጮች ምዝገባ በ 6 ዞኖች ና በ5 ልዩ ወረዳዎች እየተካሄደ ነው።

በክልልነት የሚዋቀሩት ዞኖች ጎፋ ፣ ጋሞ፣ ደቡብ አሞ፣ ወላይታ፣ ኮንሶ እና ጌዴኦ ሲሆኑ፤ 5 ልዩ ወረዳዎችም የዚሁ አካል ይሆናሉ። እነሱም፤ ቡርጂ ፤ ባስኬቶ ፤ አሌ ፤ ደራሼ እና አማሮ ናቸው ብለዋል።

በጎፋ ዞን ለደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ምስረታ ሕዝበ ውሳኔ ለመስጠት በ987 የምርጫ ጣቢያ አስተባባሪዎች እና በ 11 መዋቅሮች ሥር ባሉት ምርጫ ጣቢያዎች ሁሉም ሕዝቦች ድምጻቸውን ለመስጠት የመራጮች ካርድ እየወሰዱ ነው። የመራጮች ካርድ አሰጣጥ ሂደቱም በከፍተኛ ሰላምና መረጋጋት ሂደት ውስጥ ነው ያለው። የምርጫ ካርድ አሰጣጥ ሥርዓቱ ሲጠናቀቅ ለደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ምስረታ ቅስቀሳ ይጀመራል። ጥር 29 ደግሞ ሕዝበ ውሳኔው ይካሄዳል ብለዋል።

ሕብረተሰቡም የራሱን ሰላም በራሱ እንዲያስጠብቅ በተደረሰው ስምምነት መሰረት ንቁ ተሳትፎ እያደረገ መሆኑን የገለጹት ኃላፊው፤ በድምጹ ዴሞክራሲያዊ መብቱን ለማስከበር እያሳየ ያለውን ቁርጠኝነት በማድነቅ ከእቅድ በላይ ለመሥራት የሚያችል አስቻይ ሁኔታዎች መኖራቸውንም አመልክተዋል።

ምርጫውን የሚታዝቡ አካላት በቂ ሥልጠና ወስደው ከወዲሁ የምርጫ ሂደቱን መከታተል መጀመራቸውን ያነሱት አቶ ካሳሁን፤ በሂደቱ ላይ ያሉት ክፍተቶችንም ለምርጫ አስተባባሪዎች በማሳወቅ እንዲታረሙ ከማድረግ አኳያ የጀመሩት እንቅስቃሴ አበረታች መሆኑንም ተናግረዋል።

# ‹‹ስነዋሪዎች ቀልጣፋ አገልግሎት መስጠት በውብ ከተማ ግንባታው ቅድሚያ የተሰጠው ተግባር ነው››

## - ከንቲባ አዳነች አቤቤ

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- አዲስ አበባን ውብ ‹‹ስማርት ሲቲ›› በማድረግ ግንባታ ሂደት የከተማዋን ነዋሪዎች እንግልት በማስቀረት ቀልጣፋ የሆነ አገልግሎት መስጠት ቅድሚያ የተሰጠው ተግባር መሆኑን ከንቲባ አዳነች አቤቤ ገለጹ። አዲስ አበባን ስማርት ሲቲ የማድረጊያ ሲምፖዚየም ትናንት ተጀምሯል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ ትናንት ሲምፖዚየሙ ሲጀመር እንደገለጹት፣ አዲስ አበባን ለነዋሪዎቿ ምቹ፣ ለኢንቨስትመንት ተስማሚና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ለማድረግ የሚያስችል የቅድመ ትግበራ ስራ ሲሰራ ቆይቷል። እየጨመረ የሚመጣውን የነዋሪዎች ፍላጎት ለማሟላት ውብ፤ ሳቢና ለሰው ልጆች ቀላልና ዘመናዊ ከተማ ለመገንባት የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ነው ብለዋል።

አገራት ቴክኖሎጂን በመጠቀም የኢኮኖሚና ማህበራዊ አቅማቸውን ፈጣን፣ ቀጣይነት ያለውና ተወዳዳሪ ማድረግ እንደቻሉ ያስታወሱት ወይዘሮ አዳነች፤ ኢትዮጵያም ፈጣን የቴክኖሎጂ እድገት እያስመዘገቡ ካሉ አገራት መካከል አንዷ ናት። በኢትዮጵያ 20 በመቶ የሚሆነው ሕዝብ በከተማ እንደሚኖር እና እስከ 2040 ዓ.ም ድረስ የከተማ ሕዝብ በሦስት እጥፍ ሊያድግ እንደሚችል መረጃዎች ያሳያሉ። እንደ አዲስ አበባ ባሉ ከተሞች ደግሞ የሕዝብ ቁጥሩ ከዚህም በላይ እንደሚጨምር ይገመታል ነው ያሉት።

‹‹የስማርት ሲቲ›› ጽንሰ ሃሳብ በጥናት ተደግፎ የአተገባበር ሂደቱ ውጤታማ እንዲሆን እየተሰራ መሆኑን የገለጹት ከንቲባዋ፤ እያደገ የሚመጣው የከተማ ዕድገት መሰረት ያደረገ ስራ መስራት አስፈላጊ ነው። ከተማ አስተዳደሩ በአጭር ጊዜ ውስጥ የከተማዋን የተጎሳቀሉ ገጽታዎች እንዲቀየሩ በማድረግ በኩል ውጤታማ ስራዎችን ሰርቷል። ነገር ግን በአገልግሎት አሰጣጥ በኩል ዘመናትን የተሻገሩ ውስብስብ ችግሮች ያሉበት በመሆኑ የ‹‹ስማርት ሲቲ›› ፕሮጀክት ለችግሮች መፍትሄ መያዙን ጠቁመዋል።


ፎቶ - አዩብ ተፈሪ

ከንቲባዋ ‹‹በስማርት ሲቲ›› ግንባታው የከተማዋን ነዋሪዎች ውጣ ውረድ፤ በአገልግሎቱ ዘርፍ ያሉ እንግልቶችን ለማስቀረት ቅድሚያ ተሰጥቶታል። ከተማዋን ለማሳደግና ለነዋሪዎቿ ምቹና ተስማሚ ለማድረግ ቴክኖሎጂ አይነተኛ መሳሪያ ነው። የስማርት ሲቲ ፕሮጀክት ከታች የሚጀመር ሳይሆን መሻሻል ያለባቸውን በማሻሻል መገንባት የሚያስፈልጋቸውን በመገንባት የሚሰራ ነው። በሂደት ላይ ያሉ የቴክኖሎጂ ስራዎች ሳይቋረጡ አዳዲስ አሰራሮችን ለመዘርጋት ትኩረት ተሰጥቶታል ብለዋል።

አዲስ አበባን ‹‹ስማርት ሲቲ›› የማድረግ ውጥን ለከተማዋ ነዋሪዎች አዳዲስ እድሎችን እንደሚያስገኝ የገለጹት ከንቲባዋ፤ ቀልጣፋ አገልግሎት እንዲያገኙ፤ የነዋሪዎችን የደህንነት ሁኔታ ማረጋገጥ፣ በመንግሥትና በከተማዋ ነዋሪዎች መካከል ትብብርንና ቅንጅታዊ አሰራርን ለማሳደግ ትልቅ እድል ነው።

አዲስ አበባን ለነዋሪዎቿ ምቹና ተስማሚ ለማድረግ የተጀመረው የስማርት ሲቲ ፕሮጀክት ግብ እንዲመታ የተቋማት ወይም የአመራሩ ድርሻ ብቻ ሳይሆን የሁሉንም ቅንጅት የሚጠይቅ መሆኑን ገልጸዋል።

የአዲስ አበባ ቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ኃላፊ ወይዘሮ ሀቢባ ሲራጅ፣ ከተማዋን ዘመናዊ ቀልጣፋ አገልግሎት አሰጣጥ ያለባት፣ በኢኮኖሚ የዳበረች፣ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የበለፀገችና ለነዋሪዎቿ ምቹ የሆነች ለማድረግ ይሰራል። በከተማዋ የዲጂታል አገልግሎት ለመዘርጋት 2 ነጥብ 2 ቢሊዮን ብር በላይ በመመደብ ለአይሲቲ ግንባታ፣ ለተቀናጀ የሶፍትዌርና ሌሎች ፕሮጀክቶችን ለመገንባት እየተሰራ ነው።

በትምህርት ቤቶች፣ በወሳኝ ኩነት ቢሮዎች፣ በቴክኒክና ሙያ ተቋማት፣ በትራፊክ ማኔጅመንትና በሌሎች ተቋማት ቴክኖሎጂን በመጠቀም አገልግሎትን በማቀላጠፍ የተጀመረውን የስማርት ሲቲ ግንባታ በዲጂታል ቴክኖሎጂ ለማሳደግ በትኩረት እየተሰራ መሆኑን ወይዘሮ ሀቢባ ገልጸዋል። በአዲስ አበባ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ፣ በአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ፣ በኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር፣ በኢትዮ ቴሌኮም ዘርፍ ስማርት ለማድረግ ጥናቶች ቀርበው ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት ተደርጎባቸዋል።

አዲስ አበባን ስማርት ሲቲ ለማድረግ ከአመት በፊት ጀምሮ የቅድመ ዝግጅት ስራዎች ሲሰሩ መቆየታቸው ይታወሳል።

# ባለሥልጣኑ ለ20 ዓመታት ሲገለገልበት የቆየውን የመንገዶች ዲዛይን ማንዋል በአዲስ ሲቀይር ነው

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- ለ20 ዓመታት ሲገለገልበት የቆየውን የመንገዶች ዲዛይን ማንዋል በአዲስ ሊቀየር መሆኑን የአዲስ አበባ መንገዶች ባለሥልጣን አስታወቀ።

የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ኢንጂነር ሞገስ ጥበቡ እንደገለጹት፤ ባለሥልጣኑ ለ20 ዓመታት ሲገለገልበት የነበረውን የመንገዶች የዲዛይን ማንዋል በአዲስ ለመቀየር ጥናት አካሂዷል፡፡ በጥናቱ ላይ ባለድርሻ አካላት የሚሰጡትን ተጨማሪ ግብዓት በመሰብሰብ አዲስ በሚቀየረው የመንገዶች ዲዛይን ማንዋል ላይ የሚካተት ይሆናል።

ላለፉት 20 ዓመታት ያገለገለው ማንዋል በርካታ ስራዎች የተሰሩበት ቢሆንም የተለያዩ ክፍተቶች እንዳሉበት በስራ ሂደት ለይተናል ያሉት ኢንጂነር ሞገስ፤ እነዚህን ክፍተቶች በሚሞላና በዘርፉ ያሉትን አዳዲስ እድገቶችና ለውጦች በማካተት አዲሱ የመንገዶች ዲዛይን ማንዋል የተዘጋጀ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ይህ የመንገዶች ዲዛይን ማንዋል የቀድሞው ያላካተታቸውን በርካታ አዳዲስ እሳቤዎች እንዳካተተም ጠቅሰዋል። በዚህም አካታች የትራንስፖርት ሥርዓትን በመዘርጋት የህብረተሰቡን ኑሮ ለማቃለል መታቀዱን ተናግረዋል።

አዲስ አበባ የሀገራችን መዲና እንደመሆኗ መጠን የሚሰራው የመንገዶች ዲዛይን ማኑዋል ያማረ እንደሚሆነ ጠቅሰው፤ ፕሮጀክቱ በዓለም ባንክ ድጋፍ የሚሰራ ሲሆን የትራንስፖርት ሴክተሩን የማሻሻል አካል መሆኑንም አመልክተዋል።

በአሁኑ ጊዜ በመዲናዋ ውስጥ እየተስተዋሉ ያሉ የመንገድ ዲዛይን ችግሮችን ለመቅረፍ የዚህ ማኑዋል መዘጋጀት ትልቅ ለውጥ የሚያመጣና በቀጣይ የሚሰሩ የመንገድ ዲዛይኖች ይሄንን መሠረት ተደረገው እንደሚዘጋጁ እንጂነር ሞገስ ተናግረዋል።

አዲስ አበባ ሌሎች ዓለም አቀፍ ከተሞች ያሉዋቸውን መንገዶች ደረጃ ለማሟላት የሚደረገውን ጥረት በከፍተኛ ሁኔታ የሚደግፍ ይሆናልም ብለዋል።


ፎቶ - ገበበ ገብሬ

**ኢንጂነር ሞገስ ጥበቡ**

እንደ ኢንጂነር ሞገስ ገለፃ ፤ የቀድሞው ማኑዋል ትኩረት የሚያደረገው የመኪኖች የትራፊክ ፍሰት ላይ ሲሆን፤ አዲሱ ማኑዋል በዓለም አቀፍ ደረጃ ከተሞች ላይ የሚሰሩ ስራዎች እንደሚያሳዩት ሰው ተኮር የሆኑ ጭስ አልባ ትራንስፖርትን ታሳቢ ያደረገ ነው፡፡ ከዚህም ባሻገር በዘላቂነት የከተማይቱን የትራፊክ መጨናነቅ ችግር የሚፈታ ማኑዋል ነው ተብሎ ይጠበቃል ።

በሚቀጥሉት ሃያ ወራት ጊዜ ውስጥ ሙሉ ለሙሉ የዲዛይን ማኑዋሎችን በማዘጋጀት ከባለድርሻ አካላት ጋር የውይይትና የሥልጠና መርሃግብር እንደሚኖር ኢንጂነር ሞገስ ጠቅሰው፤ በአጠቃላይ ሥልጠናውን ጨምሮ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ፕሮጀክቱ እንደሚጠናቀቅ ተናግረዋል።

የመንገዶች ዲዛይን ማንዋል ፕሮጀክት የሚያከናውነው የዳራል ሀንድሳ አማካሪ ግሩፕ ጄኔራል ማናጀር አቶ ደባይ ሚሊዮን እንደገለጹት፤ አማካሪ ግሩፑ በዚህ የስራ ዘርፍ ከፍተኛ ልምድ አለው፡፡ ይህንን ፕሮጀክት በሶስት ዙሮች በመከፋፈል በተያዘለት ጊዜ ለማጠናቀቅ ቅድመ ዝግጅት ተደርጓል።

# ከሰላም ስምምነቱ ማግስት የሚከበረው በዓል ተቀዛቅዞ የነበረውን የቱሪዝም ኢኮኖሚ ያነቃቃል

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- ከሰላም ስምምነቱ ማግስት የሚከበረው የገናና የጥምቀት በዓል ተቀዛቅዞ የነበረውን የቱሪዝም ኢኮኖሚ እንዲነቃቃ እንደሚያደርግ የቱሪዝም ሚኒስቴር አስታወቀ።

በቱሪዝም ሚኒስቴር የግብይትና ፕሮሞሽን ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ወይዘሮ ሰላማዊት ዳዊት ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ኃይማኖታዊ ፌስቲቫሎች የቱሪስት መዳረሻዎችን ለማስተዋወቅ፣ የውጭ አገር ቱሪስቶች ወደ አገር ውስጥ ገብተው እንዲጎበኙ ለማነሳሳት እና የአገር ውስጥ ቱሪዝምን ለማነቃቃት ያስችላሉ።

ትውልደ ኢትዮጵያውያንና የሌሎች አገራት ዜጎች ወደ ኢትዮጵያ መጥተው እንዲጎበኙ ከሚጋበዙባቸው ወቅቶች አንዱ የገናና የጥምቀት ፌስቲቫል አንዱ መሆኑንም ጠቁመዋል።

እንደ ሚኒስትር ዴኤታዋ ገለጻ፤ ባለፈው አመት በገናና በጥምቀት በዓል ከመቶ ሺ በላይ ቱሪስቶች ወደ አገር ውስጥ ገብተው ፌስቲቫሎችን ተካፍለዋል፣ የቱሪስት መዳረሻዎችን ጎብኝተዋል።

ባለፈው አመት እንደ አገር ብዙ ፈተናዎች ባሉበት የገናና የጥምቀት ፌስቲቫል ተከብሯል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ ዘንድሮ የሰላም ስምምነት በተደረገበት ማግስት የሚከበሩ የጥምቀትና የገና ፌስቲቫሎች በርካታ ቱሪስቶች እንደሚታደሙ ያደርጋል ብለዋል።

በአካባቢዎቹ ኤሌክትሪክ መሰረተ ልማትን ጨምሮ ሌሎች መሰረተ ልማቶች በተሟላ መልኩ እየተስተካከሉ ስለሆነ ወደ ኢትዮጵያ መጥተው እንዲጎበኙ ተነሳሽነት የሚፈጥር መሆኑንም ገልጸዋል።

ዳያስፖራውና ከተለያዩ የዓለም አገራት የተውጣጡ ቱሪስቶች ወደ ተለያዩ የአገራችን ክፍሎች በመንቀሳቀስ የቱሪስት መዳረሻዎችን የሚጎበኙበት እድል ከባለፈው አመት የተሻለ አጋጣሚ መሆኑን የጠቆሙት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ የቱሪዝም ሀብት የሚንቀሳቀሰው በቱሪስት መስብ ቦታዎች የሰዎች እንቅስቃሴ ሲኖር ነው ብለዋል። ስለዚህ ከአገር ውስጥም ከውጭም ሰዎች መጥተው


ፎቶ - ፀሐይ ንጉሤ

**ወይዘሮ ሰላማዊት ዳዊት**

ጉብኝት የሚያደርጉበት ሁኔታ መፈጠሩ የቱሪዝሙን ኢኮኖሚ በማሳደግ ያለው ሚና ከፍተኛ ነው።

አንድ ቱሪስት ከውጭ ሲመጣ በሚደርስባቸው አካባቢዎች የመኝታ፣ የትራንስፖርት፣ የመዝናኛ አገልግሎት ይፈልጋል። በተጨማሪም የቱሪዝም ምርቶች ተብለው የሚጠሩትን በመዳረሻው ሁሉ ለማስታወሻነት ይገዛል። ስለዚህ የቱሪዝም ኢኮኖሚው የማንቀሳቀስ እድሉ ከፍተኛ ነው ሲሉ ወይዘሮ ሰላማዊት ተናግረዋል።

ወይዘሮ ሰላማዊት በኮቪድና በግጭቱ ሳቢያ ተቀዛቅዞ የቆየው የአገልግሎት ዘርፍ የስራ ዕድል በመፍጠር ነው። ቱሪስቶች የገናና የጥምቀት ፌስቲቫልን ለመታደም ወደ ኢትዮጵያ የሚመጡ ስለሆነ በዘርፉ ላይ ከፍተኛ የኢኮኖሚ መነቃቃት ይፈጥራል። ይህም ለአገር ኢኮኖሚ ዕድገት ፋይዳው ላቅ ያለ ነው። ስለሆነም ይህ ተግባር ሁልጊዜም ሊለመድና ሊበረታታ የሚገባው ነው ብለዋል።

ቱሪስቶች ወደ አገር ውስጥ ገብተው እንዲጎበኙ ያሉ የቱሪስት መዳረሻዎችን በቱር ኦፕሬተሮች አማካኝነትና በልዩ ልዩ ዘዴዎች የማስተዋወቅ ስራ እየተሰራ ነው። ለዚህም የሰላም ስምምነቱ ትልቅ እድል ሰጥቷል። ለውጤታማነቱ ከክልሎች ጋር በቅንጅት እየተሰራ ነው ሲሉም ሚኒስትር ዴኤታዋ ገልጸዋል።

አቅሙ የፈቀደ ዳያስፖራ ሁሉ በየአመቱ እየመጣ አገሩን እንዲጎበኝ ይጠበቃል። በገናና ጥምቀት የኃይማኖታዊ ፌስቲቫልን ከማክበር ባሻገር ያሉትን አዳዲስና ነባር የቱሪስት መስቦች ለጉብኝት ዝግጁ በማድረግ የማስተዋወቅ ስራ እየተሰራ መሆኑንም ሚኒስትር ዴኤታዋ ተናግረዋል።

# የስሁል ሽሬ ጠቅላላ ሆስፒታል ነጻ የህክምና አገልግሎት...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

እየሰጠ መሆኑን የሆስፒታሉ ሚዲካል ዳይሬክተር አስታወቁ።

የስሁል ሽሬ ጠቅላላ ሆስፒታል ሚዲካል ዳይሬክተር ዶክተር ፍስሃጽዮን ገብረመድህን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፣ ሆስፒታሉ ከሰላም ስምምነቱ ወዲህ አገልግሎት የጀመረ ሲሆን፣ የድንገተኛና የተኝቶ ህክምና፣ የወሊድ አገልግሎት፣ የተመላላሽ ህክምና፣ የቀዶ ጥገና አገልግሎት በመስጠት ማኅበረሰቡን በነጻ እያገለገለ ይገኛል።

ሆስፒታሉ አገልግሎት መስጠት ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ እስካሁን ከሶስት ሺህ በላይ ተመላላሽ ታካሚዎችንና ከአንድ ሺህ በላይ የድንገተኛ ታካሚዎችን በነጻ ያከመ ሲሆን፣ ከ20 ሰዎች በላይ ነጻ የቀዶ ተደርጎላቸዋል፡፡ 57 ነጻ የወሊድ አገልግሎም ተሰጥቷል።

ዶክተር ፍስሃጽዮን እንዳሉት፣ በኢትዮጵያ ጤና ሚኒስቴር በተቀመጠው አቅጣጫ መሰረት ሁሉም ህክምና እየተሰጠ ያለው በነጻ ነው። የጤና ባለሙያዎችም ክፍያ እየተፈጸመላቸው ይገኛል።

በግጭቱ ምክንያት ሕዝቡ የሚያገኘው የህክምና አገልግሎት በቂ እንዳልነበርና የመድሃኒት እጥረት እንደነበር ገልጸው አሁን ላይ የተሻለ ህክምና በነጻ መስጠት መቻሉን አስታውቀዋል።

በቀጣይ ለታካሚዎች የአንቡላንስ አገልግሎት እንዲሰጥ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል ያሉት ሜዲካል ዳይሬክተሩ፤ ሆስፒታሉ ወደ ሙሉ አገልግሎት እንዲመለስ የህክምና መሳሪያና የቢሮ እቃዎች በበቂ ሁኔታ መሟላት እንደሚፈልግ ገልጸዋል።

የነጻ ህክምና ተገልጋይ የሆነው ወጣት ተክላይ ዓለም፣ እግሩ ላይ በደረሰበት አደጋ በሆስፒታሉ የቀዶ ጥገና ተደርጎለት ወደ ጤንነቱ እየተመለሰ መሆኑንና ይህም የሰላም ስምምነት በመኖሩ የተገኘ እድል እንደሆነ ገልጿል።

ሌላኛው ታካሚ አቶ ጐይቶም ወልደኪዳን፣ "የህክምና አገልግሎት ባለማግኘት ቤት ውስጥ በባህላዊ መንገድ ስታከም ቆይቼ ሰላም ከተፈጠረ ወዲህ ወደ ሆስፒታሉ መጥቼ ነጻ የቀዶ ጥገና አኘቻለሁ በዚህም ደስተኛ ሆኛለሁ። ሰላሙ ቀጣይነት እንዲኖረው ሁሉም አካል ከልብ ሊሰራ ይገባል" ብለዋል።



"ታካሚ ወደ ሆስፒታል መጥቶ በመድሃኒት እጥረት ተመልሶ ሲሄድ እንደ ጤና ባለሙያ እናዝን ነበር። አሁን ሁሉ ነገር ተቃራኒ ሆኖ የታመመው ህክምናና መድሃኒት በነጻ አግኝቶ ሲሄድ ልዩ የደስታ ስሜት እየተሰማን ነው" ያለችው የስሁል ሆስፒታል ፋርማሲስት ኤልሳ ገብረስላሴ ናት።

ፋርማሲስቷ፣ ሰላም ሲኖር ቅድሚያ ተጠቃሚ ሕዝብ ነው። ሰላም ሲጠፋም የሚጐዳው ሕዝብ ነው። በማለት፤ የተገባው የሰላም ስምምነት ለሕዝቡ ሲባል ዘላቂ እንዲሆን ቁርጠኝነት እንደሚያስፈልግ ተናግራለች።

ጠቅላላ ሆስፒታሉ ለሽሬ ከተማና ዙሪያዋ ላሉ አንድ ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ዜጐች አገልግሎት የሚሰጥ ሲሆን፣ በአሁኑ ወቅት ተፈናቃዮችን ጨምሮ ሁለት ሚሊዮን ለሚጠጋ ሕዝብ አገልግሎት የመስጠት አቅም ይዞ እየሰራ ነው።

# በትግራይ ክልል አስቸኳይ የሰብዓዊ ድጋፍ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ተገኝተዋል።

በትግራይ መሰረታዊ አገልግሎቶች ዳግም እንዲጀመሩና ሰብአዊ ድጋፍ ተደራሽ በማድረግ የመንግሥትን ቁርጠኝነት ያደነቁት ልዩ መልእክተኛው የመንግሥትና የሕወሓት አመራሮችም ለሰላም ስምምነቱ ላደረጉት ቀና ተግባር አመስግነዋል።

በሰሜን ኢትዮጵያ ሰብዓዊ ድጋፍ ያለ ገደብ ማቅረብ፣ መሰረታዊ አገልግሎቶችን መልሶ ማስጀመርና ዘላቂ ሰላም ማስፈን የሰላም ስምምነቱ አካል እንደነበርም አስታውሰው ስምምነቱን ተከትሎ መንግሥት በገባው ቃል መሰረት ሁሉንም ነገሮች ተፈፃሚ በማድረግ ላይ በመሆኑ አመስግነዋል።

በትግራይ ኤሌክትሪክ፣ ባንክ፣ ቴሌኮሙኒኬሽን፣ መንገድ፣ እንዲሁም ሌሎች መሰረታዊ አገልግሎቶች በአጭር ጊዜ አገልግሎት መስጠት መጀመራቸው የሚደነቅ መሆኑንም ገልጸዋል።

የሰላም ስምምነቱን ተከትሎ መንግሥት የሚታዩ አወንታዊ እርምጃዎችን እየወሰደ መሆኑን ጠቅሰው በአፈ ጉባኤ ታገሰ ጫፎ የተመራ የመንግሥት ከፍተኛ የስራ ሃላፊዎች ልዑክ በመቀሌ ያደረገው ጉብኝትም የመንግሥትን ቁርጠኝነት ያረጋገጠ ነው ብለዋል።

የአፍሪካ ህብረት፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ የሁለቱ ወገኖች ሲቪልና ወታደራዊ አመራሮች ለዚህ ውጤት መምጣት ድርሻው የጎላ በመሆኑ ምስጋና ይገባቸዋልም ነው ያሉት ልዩ መልእክተኛው።

የቀድሞው የኬንያ ፕሬዚዳንት ኡሁሩ ኬንያታ፤ ሁሉም የትራንስፖርት መተላለፊያዎች ለአስቸኳይ ሰብዓዊ እርዳታና መሰረታዊ አገልግሎቶች ክፍት መደረጋቸውን አረጋግጠናል ብለዋል።

በትግራይ ክልል የሰብዓዊ እርዳታን ጨምሮ የአየር ትራንስፖርት፣ መንገድ፣ ባንኮች፣ የኤሌክትሪክና ሌሎችም አገልግሎቶች ዳግም ስራ መጀመራቸው የሚደነቅ መሆኑንም ገልጸዋል።

"ለዚህ ውጤት የሁለቱ ወገኖች አመራሮች ምስጋና ይገባቸዋል፣ እኛም ትብብራችንን አጠናክረን እንቀጥላለን" ሲሉ ተናግረው የሰላም ስምምነቱ አፈፃፀም ለአፍሪካ ችግር አፍሪካዊ መፍትሔ መስጠት እንደሚቻል ሁነኛ ማሳያ መሆኑንም ገልጸዋል።

የፍትህ ሚኒስትሩ ዶክተር ጌዲዮን ጢሞቲዎስ በበኩላቸው፤ መንግሥት የሰላም ስምምነቱን ተከትሎ በገባው ቃል መሰረት ሁሉንም ነገሮች ተፈፃሚ እያደረገ መሆኑን ተናግረዋል።

በቀጣይም በሁሉም መስክ በቁርጠኝነት የሚሰራ መሆኑን አረጋግጠው የሰላም ስምምነቱ አፈፃፀም ለአፍሪካ ችግር አፍሪካዊ መፍትሔ መስጠት እንደሚቻል ማሳያ ነው ብለዋል።

የሕወሓት ከፍተኛ አመራር አቶ ጌታቸው ረዳ፤ በትግራይ የሰብዓዊ ድጋፍ አቅርቦቱን ጨምሮ የሰላም ስምምነቱ በሁለቱም ወገኖች ዘንድ ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑን አረጋግጠዋል።




# ርዕሰ አንቀፅ

## ስልጡን ፖለቲካ ሁሌም ለሰላም ቅድሚያ ይሰጣል!

የአንድ ሀገርና ሕዝብ የነገ ብሩህ ተስፋ በተጨባጭ መሰረት የሚያደርገው ሰላምን ነው። ያለ ሰላም ስለአንድ ሀገር ነገዎች ቀርቶ ሕልውና ማሰብ አይቻልም። ለዚህ ደግሞ ትናንት ያጋጠመን የሰላም እጦት የቱን ያህል ለህልውናችን አደጋ ሆኖ እንደተፈታተነን ለማሰብ የሚከብድ አይደለም።

በርግጥ ለረጅም ዘመናት ይዘነው የመጣነው ኋላቀር የፖለቲካ አስተሳሰብና አስተሳሰቡ የፈጠረው የሴራና የመጠላለፍ ፖለቲካ እንደ ሀገር በየዘመኑ ትውልዶችን ብዙ ዋጋ አስከፍሏል። ሀገሪቱን የደም ምድር፤ ህዝቦቿን የድህነትና የጉስቁልና ተምሳሌት እንዲሆኑ አድርጓቸዋል።

አለመግባባቶችን ጦር ሰብቆ በኃይል የመፍታት የጦረኝነት ባህል፤ ባህሉ የወለደው እልኸኝነትና ነገሮችን በአሸናፊ ተሸናፊ ትርክት ዘግቶ የመውጣት መሻት ፤ ዘመናት ተሻግረው ዛሬም የዚህ ትውልድ ፈተና ሆነው ትውልዱን ዋጋ አስከፍለውታል።

ትውልዱ በዘመናዊ አስተሳሰብና አስተሳሰቡ በሚወልዳቸው መርሆዎች ራሱን ለመግራት የሚያደርገው ጥረት የሚፈልገውን መስዋእትነት ለመክፈል /በማወቅም ይሁን ባለማወቅ/ አለመቻሉ ጥረቱን በተጨባጭ አካል ለብሶ ለሀገርና ለሕዝብ የሚጠበቀውን በረከት ይዞ እንዳይመጣ አድርጎታል።

ከቋንቋ ባለፈ ተስፋ እንደተጣለበት ዘመናዊ ትውልድ ፤ ሀገርና ሕዝብን ወደ አዲስ የታሪክ ምዕራፍ ማሻገር የሚያስችል፤ ለራሱ የታመነና ለመጪው ትውልዶች ጭምር የሚታመን ኃላፊነት የሚሰማው እንዲሆን አላስቻለውም።

በተለይም ራሱን ፖለቲከኛ አድርጎ የሰየመውና የተለያዩ የፖለቲካ አመለካከቶችን አንግቦ ወደ ሀገራዊ የፖለቲካ ገበያው የወጣው ትውልድ ለፖለቲካው ገበያው ስኬት ሀገራዊ ሰላም አልፋና ኦሜጋ መሆኑን በአግባቡ ማስተዋል ተስኖት ራሱንም ሆነ ሀገርን ያልተገባ ዋጋ አስከፍሏል።

የትውልዱ የፖለቲካ እውቀቶች ትናንትን በተጨባጭ ከማረም ያልተነሱ፤ ከዛ ይልቅ ባልታረመ የፖለቲካ ባህል ላይ የተዘሩና የበቀሉ በመሆናቸው ፍሬ አልባ ሆነዋል። መላው ሕዝብንም ግራ በሚያጋባ እንቆቅልሽ ውስጥ እንዲያልፍ አድርጎታል።

ትውልዱ /አሁን ያለው ፖለቲከኛ ትውልድ / የቱንም ያህል የዘመናዊ እውቀትና መገለጦች ባለቤት ቢሆንም ፤ መድረኮችን ከነዚህ እውቀቶች በሚቀዱ ዲስኩሮች ቢያጣብብም ፤ ሀገራዊ ሰላምን በቀዳሚነት አጀንዳ ማድረግ የተሳናቸው ብዙ በመሆናቸው ከቋንቋ ያለፈ ትሩፋት ማምጣት አላስቻሉም።

እነዚህ መድረኮችን የሚያጣብቡ ዲስኩሮች እየቆዩ ሲሄዱ፤ የሕዝባችንን የነገ ተስፋ ከማቀጨጭ ባለፈ ብዙ ዋጋ ከፍሎ ባስተማራቸውና ለብዙ ማዕረግ ባበቃቸው የአብራኩ ክፋዮች ላይ የነበረውን መተማመን እንዲያጣና ትናንቶችን ናፋቂ እንዲሆን አድርገውታል። ለዚህ ደግሞ ላለፉት አራት አመታት በሀገሪቱ የፖለቲካ ገበያ የነበረውን እውነታ በአግባቡ ማጤን ተገቢ ነው።

ባለፉት አራት አመታት በሀገሪቱ የሽግግር የፖለቲካ ገበያ አትራፊ ሆኖ ለመገኘት አንቱ የተባሉ የዘርፉ ስመጥር ምሁራን ሳይቀሩ፤ ከገበያው ከመርህ ውጭ ሀገራዊ ሰላምን በመናጥ ፤ በሀገራዊ ሰላም ለመሸቀጥ በብዙ ሲሞክሩ ማስተዋል ችለናል።

አንዳንዶች የፖለቲካ ገበያውን ፍጹም በኃይል በማተራመስ በሚፈጠር የፖለቲካ ክፍተት ፍላጎታቸውን ለማሟላት የሄዱበት የጥፋት መንገድ መላው ሕዝባችን ከተመሳሳይ ትናንቶች የከፋ እና ያልተገባ ዋጋ እንዲከፍል አስገድደውታል።

ሕዝባችን ከፍ ያለ ተስፋ ሰንቆ፤ ብዙ ዋጋ ከፍሎ የጀመረው ለውጥ እንደ ቀደሙት ዘመናት የለውጥ ተሞክሮዎች፤ በደም ተጀምሮ በደም እንዲያበቃ ፤ በብዙ ተስፋ ተጀምሮ ቅዠት በሚመስል መንገድ ወደ ፍጻሜው እንዲጓዝ በብዙ ተግተዋል።

እነዚህ ኃይሎች የፖለቲካ ገበያውን እንዳይረጋጋ በማድረግ ተጠቃሚ ለመሆን የሄዱበት መንገድ አንድም ለገበያው መርህ የተገዛ አለመሆኑ አትራፊ አላደረጋቸውም፤ ከሁሉም በላይ በሀገራዊ የፖለቲካ ገበያው ውስጥ ተፈጥሮ የነበረውን መልካም አጋጣሚ ችግር ውስጥ በመክተት የለውጥ ጉዞው አዝጋሚ እንዲሆን አድርገውታል።

ይህ ራስን ቀድሞ በፖለቲካ ገበያ መርህ ካለመግራት የሚመነጨው የፖለቲካ ባህላችን፤ ብዙ ትናንቶችን እንዳሳጣን ፤ ከዛም ባለፈ እንደ ሀገርና ሕዝብ ያልተገባ ዋጋ እንዳስከፈለን ተረድቶ ለመታረም ለፖለቲከኞቻችን ይህ የተሻለው ጊዜ እንደሆነ ይታመናል።

ፖለቲከኞቻችን ብዙ ተስፋ ሰንቀን በጀመርነው ለውጥ ማግስት እንደ ሕዝብና ሀገር ያስከፈሉን ዋጋ ከልብ ሊጸጽታቸው ይገባል ፤ ጸጸታቸው እንደ ሰው አዕምሯቸው ለሚጠይቃቸው ጥያቄ ምላሽ ከመሆን ባለፈ ተመሳሳይ ስህተት ላለመስራት ፤ አልያም ከፖለቲካው ገበያው ራሳቸውን እስከማግለል የሚደርስ ሊሆን ይገባል!


ኢፕድ

**አዲስ ዘመን**

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


**ነፃ ሃሳብ**

**ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::**

## የሰላም እሴቶቻችን እና ሁለንተናዊ ፋይዳቸው

ግርማ መንግሥቴ

በሁላችንም አካባቢዎች ሊስፋፉ፣ ሊዘወተሩ . . . የሚገባቸው፤ በችግር ፈችነታቸውና መሰረታዊ የሰላም ምንጭነታቸው ተገቢው ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ማህበረ-ባህላዊ እሴቶች አሉ። እነዚህ እሴቶች ሀገርን እንደ ሀገር ዘመናት ተሻግራ እንድትመጣ ያስቻሉ ከፍ ያሉ ብሔራዊ አቅሞች ናቸው።

እነዚህ እሴቶቻችን ዛሬም ቢሆን ከዘመናዊው የችግር አፈታት ዘዴ /ጥበብ/ ባልተናነሰ መንገድ በግለሰቦች በቡድኖችና በማህበረሰቦች መካከል የሚፈጠሩ ግጭቶችን በመፍታት ሰላም በማስፈን ሂደት ውስጥ ያላቸው ስፍራ የጎላ ነው። ከነዚህ እሴቶቻችን መካከልም አንዱ ጎሜ ነው።

የቱባ ባህላዊ እሴቱ ዋና ባለቤት በሆነው የጎፋ ሕዝብ ብያኔ መሰረት፣ "ጎሜ" ማለት እርምት (መታረም) ማለት ሲሆን፣ የጎፋ ሕዝቦች በሁለት ወይም በብዙ ሰዎች መካከል የተፈጠረን አለመግባባት ዳግም እንዳይነሳና በዘላቂነት በመፍታት የነገ መጻይ ዕድል ተስፋቸውን በጋራ የሚያልሙበት የፍትህ ሥርዓት ነው፡፡

ከሁሉም በላይ ደግሞ፣ ጽንሰ ሀሳቡን የበለጠ ለመረዳት የተወላጁንና ፍፁም ኢትዮጵያዊያን፣ የአሰፋ ጨቦን ስራዎች ማንበብ ጠቃሚ ነው። ጋሽ አሴ ነፍሱን ይማረውና ውሸት (መዋሸት) ጎሜ መሆኑን ከመናገር ጀምሮ ከበቂ በላይ ጽፏል፤ መክሯል፤ ዘክሯልም። ግጭት ይወገድ፣ ሰላም ይሰፍን ዘንድም ሕይወቱን ሙሉ፤ ያለ ምንም መታከት ተሟግቷል። (ጋሽ አሴ እናመሰግንሃለን!!!)

በስፋት ሲነገር እንደ ነበረው፤ በተግባርም እንደታየው፣ የጎፋ ዞን ሕዝቦች የውስጥ አንድነትን የሚያጠናክር "ጎሜ"ን የሚያወጣ የዕርቅ ሥነ ሥርዓት አላቸው፡፡"ጎሜ ማውጣት" ማለት ኃጢያትን መናዘዝ ወይም እርምን ማውጣትና የነገን ተስፋ በመልካም መሠረት ላይ ማቆም ነው።

ዕርቁም የሚከናወነው በተለያዩ ቦታዎች፣ በመንግሥት የሥራ ኃላፊነት ከነበሩ የአካባቢው ተወላጆች ጋር ነው። ይህ ደግሞ፣ እነሆ ቀጥሎ ዛሬ እጅግ ወሳኝ በሆኑ ሁኔታዎች ሁሉ አገራዊ መፍትሄ፤ የሰላም

> **የጎፋ ዞን ሕዝቦች የውስጥ አንድነትን የሚያጠናክር «ጎሜ»ን የሚያወጣ የዕርቅ ሥነ ሥርዓት አላቸው፡፡«ጎሜ ማውጣት» ማለት ኃጢያትን መናዘዝ ወይም እርምን ማውጣትና የነገን ተስፋ በመልካም መሠረት ላይ ማቆም ነው**

አስኳል በመሆን ላይ ሲሆን፣ ለዚህ ማሳያው ደግሞ (ጠላቶቻችን እየደገሱልንና ሲደግሱልን እንደ ነበሩት ሳይሆን) ያለ ምንም ጣልቃ ገብነት በመንግሥትና ሕወሓት መካከል እየወረደ ያለው እርቅና እየሰፈነ ያለው ሰላም ነው። ወደ ጎሜ እንመለስ።

በአካባቢው የሚገኙ የተለያዩ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት በአገር ሽማግሌዎች የሚመራው የጎሜ ሥነ ሥርዓት የሕዝብ ለሕዝብ ቅርርብን ከማጠናከር ባሻገር፤ ዘላቂ ሰላምንና ልማትን የማረጋገጥ ሚና አለው። ማለትም ፋይዳው ግጭትን ማስወገድ ተብሎ ብቻ የሚታለፍ አይደለም። ፋይዳው ከማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ዘርፎችም ባለፈ አስተዳደራዊ፣ ፖለቲካዊ ... ችግሮችን እስከ መፍታት ድረስ የሚዘልቅና በተግባርም የተፈተነ ነው።

### ፖለቲካዊ ፋይዳ

ይህንን ንኡስ ርእስ ተጨባጭ ለማድረግ አንድ ግዙፍ ሁነትን ብቻ መጥቀሱ፤ እንዲሁም፣ በደቡብ ሕዝብና ክልሉን በሚያስተዳድረው ፓርቲ መካከል የሆነውን (ጥር 2011 ዓ.ም) ብቻ ማየቱ በቂ ነው። (ይህ ደግሞ፣ ዝቅ እያልን እንደምናየው፣ በሌሎች የአገራችን ክፍሎችም እየተስፋፋ፣ ሰላምና እርቅ እየወረደና እየሰፈነ ነውና እሴቶቻችን የዋዛ አይደሉም ማለት ነው።)

ቀደም ባለው ጊዜ የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ደኢሕዴን) ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባልና የአዲስ አበባ ኢህአዴግ ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ተስፋዬ ቤልጂጌ "በወቅቱ ለሕዝብ ጥያቄ ምላሽ ባለመስጠቱ፣ በአግባቡ ባለማገልገላችንና ሕዝብን በማስቆጣታችን ይቅርታ አድርጉልን" በማለት ፓርቲው በአባላቱ አማካኝነት ሕዝቡን ይቅርታ መጠየቁን፤ በሥነ ሥርዓቱ ላይ የተገኘው ሕዝብም ይቅርታውን መቀበሉን ሰምተናል።

በጎሜ ስነስርአት መሰረትም ሕዝቡ ይቅርታ ስለማድረጉና ችግሩ ዳግም እንዳይነሳ፤ ዘላቂ ሰላምን ለመገንባትና ኅብረትን ለማጠናከር በማሰብ የጋሻና ጦር ስጦታ ለአቶ ተስፋዬ ያበረከተላቸው መሆኑንም በወቅቱ በተለያዩ መገናኛ ብዙሃን ከተላለፉት ዜና ዘገባዎች ተረድተናል። ይህ ማለት፣ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርአት እስከ ክልሉ ገዢ ፓርቲ ድረስ የዘለቀ፣ በፖለቲካና አስተዳደራዊ ጉዳዮች ሁሉ ሳይቀር መፍትሄን የሚሰጥ ባህላዊ እሴት ነው ማለት ነው።

ይህ የሚያሳየን ወይም የሚያስተምረን አቢይ ጉዳይ ቢኖር ልክ እንደ ጎሜ ሁሉ በገዳውም ሆነ በሰሜኑ በየአገራችን አካባቢዎች (ጎጃም፣ ጎንደር፣ ትግራይ...) የሚታወቀው "የአባት ባህላዊ ሕግ ሥርአት" ("የኢትዮጵያ የሀገር በቀል የአስተዳደር፣ የሕግና የፍትሕ ሥርዓቶች ማውጫ ቅጽ 1"ን ይመለከቷል) እንዲሁም በሌሎች እሴቶቻችን ዘንድ ተግባራዊ ሊደረግ የሚገባው መሆኑን ነውና መታደል ነው። የኦሮሞ ባህላዊ እሴት ወደ ሆነው ገዳ ስርአት እንዝለቅና አንድ ጉዳይ ብቻ እናንሳ።

ባይሳ ኩማ ጎንፋ (Baay'isaa Kumaa Gonfaa) የተባሉ የድረገጽ ጦማሪ በማህበራዊ ድረ-ገጻቸው ላይ፡-የኦሮሞ ፍልስፍና ምንጩ ገዳ ነው፡፡ የዓለም ቅርስ ከሆነው ታላቅ ስርዓት የሚቀዳው ፍልስፍና ፖለቲካዊ፤ ኢኮኖሚያዊ፤ ማህበራዊ ሕይወትና አስተዳደራዊ ጥበብን፤ የግጭት አፈታትና ጠላትን መመከትን ያሰለጥናል፡፡

በገዳ ባህል፤ ወግና ስርዓት የሰለጠነ ልጅ ሆደ ሰፊነትን፤ ማቀፍና መደመርን አሳምሮ ያውቃል። እንቅፋትን እንዴት እንደሚያነሳና ጠላት ሆኖ የመጣበትን እንዴት እንደሚመክት፤ በጦር ውሎ የማረከውን እንዴት ኦሮሙማን እንደሚያላብሰው ያውቃል፡፡ ኦሮሞ ሲጀመር ጠላትነትና ምቀኝነት ውስጡ ቢኖር የማረከውን ልጁ አያደርግም፡፡

**የሰላም እሴቶቻችን... ወደ ገጽ 6 ዞሯል**

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ

# የሰላም እሴቶቻችን እና...

ከገጽ 5 የዞረ

ምሎና ተገዝቶ ከአብራኩ ከተከፈለው እኩል ማንነቱን አያወርስም፡፡ በመሰረቱ በአፋን ኦሮሞ ውስጥ ምቀኝነትን በአማርኛ እንደምናውቀው አሳምሮ የሚገልፅ ቃል አይገኝም፡፡ ምክንያቱም የለበትምና፡፡ ከላይ ርእስ አድርጌ የተጠቀምኩት ብሂል (“ኦቱማ ሞርቱን ሞርቱ ሆርቱን ሆርቲ ... ሟርተኞች ኅሜ እያያዙ ቅኖች ባለጠግነትና ፀጋቸው ይበዛል!!!” የሚለውን ማለታቸው ነው) የኦሮሞ አባቶች ስነቃል ነው፡፡ ሟርተኞች ኅሜ ይዘው ቢውሉ ቢያድሩ ቅኖች ባለጠግነትና ፀጋቸው ይበዛል በሚል እንድምታ ሊፈታ ይችላል።

ይህን ሀሳብ ሳነሳ ኦሮሞ በመሆኔ ይህንን ሕዝብ ከውሃ የጠራ፤ ከፀሐይ ብርሃን የላቀ ጥቅምና ደረጃ እየቸርኩት አይደለም፡፡ ገዳ እንዲህ ልጁን ሊያሳድግ ግድ ስለሆነ እንጂ፡፡ በእርግጥ ከባህሉ የሚያፈነግጥ፤ ከአባቱ ትእዛዝ ውጭ የሚሆንና የእናቱን ማጀት የሚያስበረብር ገልቱም አይፈጠርም ማለቴ አይደለም፡፡ እንዲህ አይነቱን ከንቱ እንዴት እንደሚገራውም ያውቃል፡፡

በጅ አልል ሲልም መፍትሄው በእጁ ነው። እናም እነሆ እንዲህ ሆነ፡፡ የአባ ገዳ ልጆች በ21ኛው ክፍለ-ዘመን ወደ ጥንት ነገራቸው ተመለሱ። ለዓለም እነሆ ብለው ሰጥተው ለራሳቸውም በባርነት እንዲማቅቁ እጣ የሆናቸውን ሰበብ ፈልገው አገኙና መፍትሄ አበጁለት፡፡

እነሆ ከመራራቅ መቀራረብ፤ ከመጠላላትና በጠላትነት ከመተያየት በሚያግባቡ ጉዳዮች ወደ መግባባት፤ ለሀገርና ለሕዝብ ጥቅም አብሮ የመቆም፤ በደልን በይቅርታ በመተላለፍ ሁሉን ስለማቀፍ፤ ለጠላት ብርቱ ክንድ፤ ለወዳጅ ማር ስለመሆን፤ ሀቅ፤ ፍትህና ወንድማማችነትን ስለማስፈን መዘመር ጀምረዋል፡፡ አድርገውታልም።

አትጠራጠሩ በዚህኛው ዘመን የኢትዮጵያ ትንሳኤ የላቀ ድል ነው፡፡ ገዳ ለወለዳቸው ልጆች በተወለዱበት ቀበሌነት መታጠር አይመጥናቸውም፤ በሚኖሩበት ወረዳና ዞናዊ ኅጠኝነትና ለኔ ብቻ ጥቅም አይገልፃቸውም። ለኔና ለኔ ብቻ የሚል ክልላዊ መታጠርም ያንሳቸዋል፡፡ ይህንን አጀንዳ ሳነሳ ማንነት፤ ባህልና ወግ እንዲሁም የሞትንለትን የቋንቋ አጀንዳ ይቀብሩታል ማለቴም አይደለም፡፡ ይልቅስ ያበለፅጉታል፡፡

የብዙ አንድነት እንጂ የመጨፍለቅ አንድነት አይገባቸውም፡፡ እንዲህ ባለው ግልፅ አስተሳሰብ ሁሉም ሕዝቦች እኩል ተጠቃሚ የሚሆኑበት አሸናፊ አስተሳሰብ ይገባቸዋል፡፡ ስለ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ብቻ ማሰብና መትጋትም አይበቃቸውም፡፡ ሩቅ መሻገር ነው ህልማቸው። ሁሉንም ደረጃና ማንነት አጠንክረው አፍሪካን ስለማግነን ማሰብ ጀምረዋልና እንግዲህ ማንም አያቆመንም ... ይልቅዬ፣ ጠላት ሆይ ከዚህ ብሩህ ዘመን መደመር ትተህ ላትዘልቀው አትብገን በሉልኝማ!!!!

በማለት ያሰፈሩትን ከዚሁ፣ እየተነጋገርንበት ካለው ኅሜ እና ፋይዳዎቹ አኳያ ማየት ይቻላል፤ ይገባልም። ወደ ጋሞዎች እንመለስና ሌሎች ባህላዊ እሴቶችን እናንሳ።

“ወጋ ኦጋ”፣ “ቱጌ”፣“ጫቆ”፣ “ኅምታ”፣ “ማካ”፣“ዮ...”

ጋሞዎች ባልና ሚስት፣ ጎረቤት ከጎረቤት ማሕበረሰብ ከማሕበረሰብ ጋር ሲጣላ የሚፈቱበት ዘመን የተሻገረ ባሕላዊ ስርዓት ያላቸው ሲሆን፤ አንዱም “ወጋ ኦጋ” ነው። መረጃዎች እንደሚያሳዩት በጋሞ ውስጥ ብቻ ከ300 በላይ ኅሳዎች ይገኛሉ። ይገኙ እንጂ ሁሉም በዚህ ስርአት ይገዛሉ። ማንም ከዚህ ስርአት በላይ ወይም ውጭ አይደለምን።

በ“ወጋ ኦጋ” ስርዓት የማይፈታ ችግር፣ የማይወርድ ዕርቅ የለም። ሁሉም ችግር ከዚህ ስርዓት በታች ነው። የወንጀልም ይሁን

**በገዳ ባህል፤ ወግና ስርዓት የሰለጠነ ልጅ ሆደ ሰፊነትን፤ ማቀፍና መደመርን አሳምሮ ያውቃል፡፡ እንቅፋትን እንዴት እንደሚያነሳና ጠላት ሆኖ የመጣበትን እንዴት እንደሚመክት፤ በጦር ውሎ የማረከውን እንዴት ኦሮሙማን እንደሚያላብሰው ያውቃል፡፡ ኦሮሞ ሲጀመር ጠላትነትና ምቀኝነት ውስጡ ቢኖር የማረከውን ልጁ አያደርግም**

የፍትሐብሔር ጉዳዮች በዚህ ባሕላዊ ስርዓት በአጭር ጊዜ፣ በትንሽ ጉልበት ይፈታሉ። በዚህ የዕርቅ ስነ ስርዓት በዳይ፣ ተበዳይ ተገናኝተው ጉዳያቸውን ያስረዳሉ። የአካባቢው ሽማግሌዎችም ቂም በሚሽር መልኩ ያስታርቋቸዋል። ሌላው “ቱጌ” ነው።

ቱጌ ማለት ያልታሰበ ችግር ወይንም ግጭት ሲፈጠር የሚፈታበት የሽምግልና ስነ ስርዓት ነው። በዛ ቀውጢ ወቅት የጋሞ አባቶች እንዳደረጉት ሁሉ ድንገተኛ ግጭት ሲነሳ አባቶች ለምለም ሳር በእጃቸው ይዘው ከፊት ለፊት ይቆማሉ። የሽምግልና ስርዓቱም ከፊት መቆም ነው። ሽማግሌዎቹ ከፊት ለፊት ቆመው ፀቡ ካልበረደ ተንበርክከው ይለምናሉ። ፀቡን በሰላማዊ መንገድ እንደሚፈቱ ቃል ይገባሉ።

በዚህ ሰዓት አባቶቹን የሚያልፍ አንድም ሰው አይኖርም። እናቶች ደግሞ በዚህ ድንገተኛ ግጭት ጊዜ መቀነታቸውን ፈትተው፣ ጡታቸውን በመያዝ ፀብ እንዳይኖር፣ ሰላም እንዲሰፍን ይለምናሉ። ፀቡ ከጠና ከተጋጩት መካከል ይተኛሉ። እናቶችን “ማሪዣም” ይሏቸዋል። ማርያም እንደ ማለት ነው።

እናቶችም ፀብ ሲመጣ “እኔን ውሰዱ፤ እኔ ማርያም ነኝ፤ ማርያምን ረግጦ መሄድ አይቻልም፤ አትጋጩ።” በማለት ይማፀናሉ። ከዚህ በኋላ ምንም አይነት ለበቀል የተዘጋጀ እጅ ቢመጣ ክንዱን ለበቀል አይዘረጋም። ይህን ቢያደርግ “ኅሜ” ነው። ኅሜ ማለት ሀጥያት፣ እርግማን ማለት ነው። የእናቶችና የአባቶች እርግማን ይደርሳል ተብሎ ስለሚታሰብ ኅሜን ደፍሮ የሚፈፅም ማንም የለም።

ከ“መረጃ ዶት ኮም” የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው፣ በጋሞ ብሔረሰብ 42 ደሬዎች (የተለያዩ ስም ያላቸው ማኅበረሰቦች) እንዳሉ ይነገራል። ደሬዎችም የራሳቸው ድንበር አላቸው። አንዱ የአንደኛውን ላለመንካት በመሀላ ቃል የታሰረ ነው። መሃላው “ጫቆ” ይባላል። ቢጋጩ እንኳን ለመዳኘት አስቀድመው ቃል ይገባሉ።

በድንገተኛ ግጭት ሞት ቢኖር በአጭር ቀን እርቅ ይፈፀማል። እርቅ ሲፈፀምም የሟችና የገዳይ ቤተሰቦች አብረው በመብላትና በመጠጣት ነው። ይህም ስነስርዓት “ኅምታ” ይባላል። የእርቅ እርድ ሲፈፀም እርዱን የሚፈፅመው “ማካ” ይባላል። ማካ ማለት ባህላዊ የጋሞ ቄስ ነው። ከታረደ በኋላ “ኮይራፍሬ” ወይም የኅሳ መሪው ከሟችና ከገዳይ ኅሳ መሪዎች ጋር በመሆን ደም እና ፈርሱን በመርገጥ ሦስት ጊዜ ዮ... ዮ... ዮ... በማለት ኅማታ አውርደው ምግቡን በጋራ ይመገባሉ።

ዮ....ማለት ሰላም አውርደናል፤ እርቅ አድርገናል ማለት ነው። ከዚህ በኋላም ቂምና በቀል የለም፤ አካኪ ዘራፍ የለም፤ ጉዳዩ በእርቅ ተሸሯልና። ታዲያ ከዚህ በላይ ባህል፣ ያልተበረዘ፣ ያልተከለሰ እሴት፣ አገር በቀል እውቀት .... ከየት ሊመጣ ይችላል? አይችልም። በመሆኑም በመላ አገሪቱ ሊሰራ፣ የጋራ እሴትም ሊሆን ይገባልና ችላ ማለቱ ይበቃል።

ይህ ቱባ ባህል ደግሞ ሁሉም እንደሚስ ማሙበት፣ ምክር ቤት ሳይፈጠር፣ ክልልና ዞን ሳይከፈል፣ ድንቅ ስርዓት በጋሞች ዘንድ እንደ ነበረ እራሱን የቻለ ማረጋገጫ ነው።

ይህ እድሜ ጠገብ ባህላዊ ስርአቱ የቱባ ባህሉን ባለቤት፣ ያለእንከን፣ እዚህ ድረስ አዝልቋልና ተጠናክሮ ሊቀጥል የግድ ይሆናል ማለት ነው። (ጋሞ በቀድሞው በጋሞ ጎፋ ጠቅላይ ግዛት ስር የነበረ፣ ቆይቶ በጋሞ ጎፋ ዞን ስር የነበረ፣ በቅርብ ደግሞ ራሱን ችሎ የጋሞ ዞን የሆነ ነው።)

ወደ ሌሎች የአገራችን ክፍሎችም ስንመጣ

**ጋሞዎች ባልና ሚስት፣ ጎረቤት ከጎረቤት ማሕበረሰብ ከማሕበረሰብ ጋር ሲጣላ የሚፈቱበት ዘመን የተሻገረ ባሕላዊ ስርዓት ያላቸው ሲሆን፤ አንዱም«ወጋ ኦጋ» ነው። መረጃዎች እንደሚያሳዩት በጋሞ ውስጥ ብቻ ከ300 በላይ ጎሳዎች ይገኛሉ። ይገኙ እንጂ ሁሉም በዚህ ስርአት ይገዛሉ። ማንም ከዚህ ስርአት በላይ ወይም ውጭ አይደለምን**

የምናገኘው ያው ሲሆን፣ የኖርነውም ሆነ እያኖረን ያለው ይሄው እድሜ ጠገቡ ባህላዊ እሴታችን ሲያደርግ በኖረውና እያደረገልን ባለው አስተዋፅኦ እንጂ፣ ባእዳን እንደሚሉት የማንረባ፣ ችግሮቻችንን እራሳችን መፍታት የማንችል ... ቀሽሞች አይደለንም።

የፌደራሉ መንግሥትና ሕወሓት ከገቡበት ማንንም የማይጠቅም ጦርነት ውስጥ ይወጡና እዚህ አሁን ያሉበት ሰላማዊ ሁኔታ ላይ ይገኙ ዘንድ ያደረጋቸው የማንም ግፊትና ተጽእኖ ሳይሆን፤ ያኖረንና እያኖረን ያለው አገር በቀል እውቀታችን፣ ማህበረ-ባህላዊ እሴታችን፣ የግጭቶች አፈታት ስርአታችን ወዘተርፈ መሆኑን ሁሉም በደማቁ ሊያስምርበት ይገባል። ጉዳዩን ትንሽ ገፋ አድርገን እንየው።

በመንግስትና በሕወሓት መካከል በተካሄደው ጦርነት አገርንና ሕዝብን ላልተፈለገ ስቃይና መስዋእትነት ተዳርጓል። ይሁን እንጂ፣ የውጭ ሀይላት ኢትዮጵያ አለቀላት፤ ዜሮ ገባች፤ ተበታተነች ወዘተርፈ እያሉ በሚያሟርቱበት ወቅት፣ ሁለቱ ሀይሎች በራሳቸው ጊዜና ፍላጎት ወደ ጠረጴዛ ዙሪያ በመምጣት ችግራቸውን በውይይት ለመፍታት፤ ልዩነቶቻቸውን በድርድር ለማጥበብ፤ ፍላጎቶቻቸውን ለሕዝብ ጥቅም ለማስገዛት ... ተስማምተው እነሆ ወደ ተግባር እያዋሉት ይገኛሉ። ዛሬ መቀሌና አዲስ አበባ የድሮ ሕይወታቸውን የጀመሩትም በዚሁ፣ በኢትዮጵያዊ መፍትሄ አማካኝነት ነው።

ይህ ፖለቲካዊም እንበለው ርእዮተ ዓለማዊ ጣጣ ዞሮ ዞሮ አገር በቀል እውቀት ላይ፣ ባህላዊ እሴቶቻችን እግር ስር ወድቋልና በእውነት ኢትዮጵያዊነት ያኮራል። ችግሮቻችንን በራሳችን መፍታት መቻላችን ያስደስታል። በተራዛሚውም “ለአፍሪካ ችግር አፍሪካዊ መፍትሄ” ማለት ይሄው ነውና ሌሎችም ይህንን የኢትዮጵያን አርአያነት ሊከተሉ ይገባል። ካላደረጉት ራሱ ኅሜ ነውና ዋጋ ማስከፈሉ የግድ ይሆናል። ከዛ በፊት ግን፣ ኅሜን ለማስወገድ መፍትሄው ኅሜን ማውጣት ነውና ኅሜን ልናወጣ የግድ ይሆናል። ቸር እንሰንብት።

# ስታላቅ ዓላማ የመፈጠርና ስመልካም ተግባር የመኖር ተምሳሌት

አንተነህ ቸሬ

ሰው ለታላቅ ዓላማና ተልዕኮ የተፈጠረ ፍጡር ነው። ይሁን እንጂ ሁሉም ሰው ይህን ታላቅ ዓላማና ተልዕኮ አውቆና ተረድቶ ዓላማውን በተግባር ይተረጉመዋል ማለት አይደለም፡፡ እንዲያውም የሰው ልጅ ለታላቅ ዓላማና ተልዕኮ መፈጠሩን ያወቁና ዓላማውን በተግባር የኖሩት ጥቂቶች ናቸው፡፡ ከራሳቸው አልፈው ለሌሎች የኖሩ/የሚኖሩ ሰዎች የሰው ልጅ ለታላቅ ዓላማና ተልዕኮ መፈጠሩ ከተገለጠላቸው ሰዎች መካከል ይመደባሉ፡፡ በአገራችንም እንዲህ ዓይነት ሰዎች አሉ።

የ‹‹አቤኔዘር ሰፖርቲንግ ኤንድ ዴቨሎፕመንት አሶሴሽን›› (Ebenezer Supporting and Development Association - ESDA) መስራችና ስራ አስኪያጅ እንዲሁም የግሎባል ፒስ ባንክ ሃሳብ አፍላቂና ስራ አስኪያጅ የሆኑት አቶ አርጋው አየለ ከራሳቸው አልፈው ለሌሎች ከሚኖሩ፣ ከራሳቸው ደስታና ስኬት ይልቅ ለሌሎች ሕይወት መቃናት ከሚተጉ ሰዎች መካከል የሚመደቡ ናቸው።

አቶ አርጋው የተወለዱት በ1965 ዓ.ም በሲዳማ ክልል ነው፡፡ በ1989 ዓ.ም የተሻለ ኑሮ ፍለጋ ወደ እንግሊዝ ለመሰደድ አስበው ዩክሬን ደረሱ። ዩክሬን ከደረሱ በኋላ ነገሮች እንዳሰቡት ሁሉ ቀላል አልሆኑላቸውም፡፡ ካሰቡበት ለመድረስ እጅግ በጣም ፈታኝ በሆነና ‹‹በምድር ላይ መራራ ሕይወትን የቀመስኩበት አጋጣሚ፣ አገሬ ውስጥ ብሞት ይሻለኝ ነበር ብዬ የተፀፀትኩበት›› ብለው በሚገልፁት ጉዞ ወደ ሀንጋሪ ሄዱ፡፡

ሀንጋሪ ደርሰው የስደተኞች ማቆያ ውስጥ ገቡ፡፡ በስደተኞች ማቆያ ጣቢያው ውስጥ የነበሩት የተለያዩ አገራት ዜጎች መራራ የሕይወት ውጣ ውረዶችን ያሳለፉ ነበሩ፡፡ በጣቢያው ውስጥ ለስደተኞች ልዩ ልዩ ድጋፎችን የሚያደርጉ ባለሙያዎች የነበሩ ሲሆን፣ አቶ አርጋው መጽሐፍ ቅዱስ ከሚያስተምረው ወጣት አሜሪካዊ ጋር መልካም ግንኙነት ፈጠሩ፤ ለትምህርቱም ልዩ ፍላጎትና ፍቅር አደረባቸው፡፡ ‹‹እንግሊዝኛ ቋንቋ በደንብ ለማወቅ ብዬ የጀመርኩት ትምህርት ወደ ውስጤ ሰርፆ ውስጤ እየተቀየረ መጣ፤ ከዚህ በኋላ በሕይወቴ ማድረግ ያለብኝ ምንድን ነው ብዬ ማሰብ ጀመርኩ›› በማለት ሁኔታውን ያስታውሳሉ፡፡

በስደተኞች ጣቢያው የነበሩት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ረዳቶቻቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናታቸውን መቀጠል እንዳለባቸው ነግረዋቸው ባደረጉላቸው ድጋፍ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ኮሌጅ ገብተው ተማሩ፡፡ መማራቸው በሕይወት ስለመኖር ምንነትና ትርጉም እንዲያውቁ አስቻላቸው፡፡

አቶ አርጋው በሕይወት የመኖርን ትርጉም ተገንዝበው ከሦስት ዓመታት የስደት ቆይታ በኋላ ወደ አገራቸው ተመለሱ፡፡ ተምረው ወደ አገራቸው የተመለሱበትን አጋጣሚ ሲገልጹት ‹‹ወደ አዕምሮዬም፣ ወደ አገሬም ተመለስኩ›› ይላሉ፡፡ በትምህርት ላይ ሳሉ የመኖሪያ ፈቃድ አግኝተው የነበረ ቢሆንም በዚያው መቅረት ግን አልፈለጉም፡፡ በኢትዮጵያ ችግረኞችን ሲመለከቱ የበለጠ ማዘን ጀመሩ፡፡ የተቸገሩ ወገኖችን መርዳት እንዳለባቸው ቢያምኑም በወቅቱ ግን ያን ለማድረግ የሚያስችል አቅም አልነበራቸውም። ሃሳባቸው ሁሉ የተቸገሩ ወገኖችን ስለመርዳት ሆኗልና የተቸገሩትን የሚረዳውን አበበች ጎበና የህፃናት ማሳደጊያ ማዕከልን ጎበኙ፡፡

‹‹አበበች ጎበና የህፃናት ማሳደጊያ ማዕከልን ስጎበኝ፣ ከዚህ በኋላ እኔም እንዲህ ዓይነት ስራ መስራት አለብኝ ብዬ ወሰንኩ›› የሚሉት አቶ አርጋው፣ ይህን ሃሳባቸውን ይዘው ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ኮሌጅ ተመልሰው ሄዱ፡፡ የአሁኑ ጉዟቸው ግን ትምህርት ብቻ ሳይሆን ሌላም መልካም ስጦታ ይዞ ጠበቃቸው። በኮሌጁ ከወደፊት የትዳር አጋራቸው ጋር ተዋወቁ፤ ትውውቃቸው ወደ ፍቅር አምርቶ በስድስተኛ ወራቸው፣ በ1997 ዓ.ም፣ ጋብቻቸውን ፈፀሙ፡፡ አሜሪካዊቷ የአቶ አርጋው ባለቤት ወይዘሮ ራሄል አየለ፣ ከ15 ዓመታቸው ጀምረው ወደ ኢትዮጵያ መጥተው የበጎ አድራጎት ስራዎችን መስራት ይፈልጉ ነበር፡፡



አቶ አርጋው አየለ

አቶ አርጋው ከባለቤታቸው ጋር ወደ አሜሪካ ሄዱ። ከአራት ወራት ቆይታ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ተመለሱ። አቶ አርጋው ወደ ኢትዮጵያ መመለሳቸው ከቅርብ ቤተሰቦቻቸው ሳይቀር ነቀፌታ ገጠመው፡፡ ‹‹እኛን መርዳት ሲገባህ እንዴት ተመልሰህ ትመጣለህ?›› የሚሉ ወቀሳዎች በረቱባቸው፡፡ ቀሪውን ዘመናቸውን የተቸገሩ ወገኖችን በመርዳት ላይ ለማሳለፍ የወሰኑት አቶ አርጋው ግን ወቀሳዎቹን ተቋቁመው ዓላማቸውን ለማሳካት ደፋ ቀና ማለታቸውን ቀጠሉ፡፡ ‹‹አቤኔዘር ሰፖርቲንግ ኤንድ ዴቨሎፕመንት አሶሴሽን›› የተሰኘውን የበጎ አድራጎት ድርጅት በሐዋሳ ከተማ በማቋቋም የሕይወት ጥሪያቸውን ለማሳካት ፈታኙን ጉዞ ጀመሩት።

በ2000 ዓ.ም ከስምንት እስከ 17 ዓመት የእድሜ ክልል ውስጥ የነበሩ 17 የጎዳና ተዳዳሪ ህፃናትን ሰብስበው በመውሰድ ቤት ተከራይተው ማኖር ጀመሩ፡፡ በ‹‹ቤተሰባዊነት›› መርህ የሚያምኑት አቶ አርጋው፣ ህፃናቱን የሚያኖሯቸው ከራሳቸውና ባለቤታቸው ጋር በአንድ ግቢ ውስጥ ነበር፡፡ ህፃናቱ ሱስን ጨምሮ በሌሎች አስቸጋሪ የሕይወት ገጠመኞች ውስጥ ያለፉ ስለነበሩ ሁኔታው ለእነ አቶ አርጋው እጅግ በጣም ፈታኝ ነበር፡፡ ‹‹ህፃናቱ የኅብረተሰቡ እንክብካቤና ፍቅር የራቃቸው ስለነበሩ ከገንዘብና ከቁስ ይልቅ ለእነርሱ የበለጠ ትርጉምና ዋጋ ያለው እንክብካቤው ነው፡፡ ትምህርት ቤት ብናስገባቸውም ከትምህርት ቤት ወጥተው ሄዱ፤ እንዲነግዱ ገንዘብ ብንሰጣቸውም ያንንም ጥለው ሄዱ፡፡ ልዩነቱ በጣም ሰፊ ነው፡፡ ስለዚህ አዕምሯቸው ስለተጎዳ ምንም ትልቅ ነገር ብታደርግላቸው የሚተረጉሙት በተቃራኒው ነው፡፡ በመጨረሻም አንዳንድ እቃዎቻችንን ሰርቀው፣ እኛ ሳናባርራቸው ራሳቸው ጠፍተው ሄዱ›› በማለት የገጠማቸውን ፈተና ያስረዳሉ፡፡

ይህ ሁኔታ ለእነ አቶ አርጋው ትምህርት ሰጣቸው። ስለሆነም ወደ ጎዳና ያልወጡ ችግረኛ ህፃናትን ለማሳደግ ወሰኑ፡፡ በሃዋሳ ዩኒቨርሲቲ መምህር የነበረ ወዳጃቸው ደቡብ ኦሞ አካባቢ ‹‹ሚንጊ›› ተብለው በማኅበረሰቡ የተፈረጁ ህፃናትን እንዲታደጉ ሃሳብ አቀረበላቸው፡፡ አቶ አርጋውም በፍጥነት ወደ ደቡብ ኦሞ በመሄድ ከአካባቢው የመንግሥት የስራ ኃላፊዎች ጋር ተነጋግረው ህፃናቱን መታደግ እንደሚችሉ ተነግሯቸው ሁኔታዎችን ለማመቻቸት ወደ ሐዋሳ በተመለሱበት ወቅት አሳዛኙና አስደንጋጩ ነገር ተከሰተ፡፡ ‹‹ሚንጊ›› ተብለው የተፈረጁት ህፃናት የባህል ሰለባ ሆነው ሕይወታቸው እንዲያልፍ ተደረገ፡፡

‹‹የሆነውን ስሰማ ወሽመጤ ተቆረጠ፤ ባለቤቴ ደግሞ ህፃናቱን የመታደግ ጥረታችን እንዲሳካ ጉጉት ስለነበራት በየደቂቃው እየደወለች ትጠይቀኝ ነበር›› በማለት የሚያስታውሱት አቶ አርጋው፣ ከፍተኛ በሆነ ንዴት ውስጥ ሆነው በየደረጃው ወዳሉ የአስተዳደር ኃላፊዎች ቢያመሩም ‹‹ሚንጊ የተባለውን ጎጂ ልማዳዊ ድርጊት አጥፍተናል›› ብለው እስከ ፌደራል መንግሥት ድረስ የውሸት ሪፖርት ያቀረቡት የስራ ኃላፊዎች ‹‹ለምን እንደዚህ ተደረገ?›› ለሚለው የአቶ አርጋው ጥያቄ ጆሮ አልነበራቸውም፡፡ ይባስ ብለውም አቶ አርጋውን ለማሳሰር ፖሊስ መደቡባቸው፡፡ የክልሉ ከፍተኛ ባለስልጣናት ‹‹አትሰሩት፣ ግን አታሰሩት›› የሚል ትዕዛዝ ስለሰጡ ለጊዜው ሳይታሰሩ ቀሩ፡፡

አቶ አርጋውና ባለቤታቸው ግን ጥረታቸውን አላቆሙም፡፡ ሌሎች በ‹‹ሚንጊ››ነት የተፈረጁ፣ ከባድ የጤና ችግር ያለባቸውን፣ ረዳት የሌላቸውንና የተጣሉ ህፃናትን እየሰበሰቡ ማሳደግ ጀመሩ፡፡ ይህ በፈተና የተሞላው ጥረታቸው ፍሬ አፍርቶ ማዕከሉ በአሁኑ ወቅት ከተለያዩ የኢትዮጵያ አካባቢዎች (ከ45 በላይ ብሄሮች) የተሰባሰቡ 130 ህፃናትን እያሳደገ ይገኛል። ከእነዚህ መካከል አስሩ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ለመሆን በቅተዋል፡፡ 120ዎቹ ደግሞ ከመዋዕለ ህፃናት እስከ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚማሩ ናቸው። በ‹‹አቤኔዘር ሰፖርቲንግ ኤንድ ዴቨሎፕመንት አሶሴሽን›› አድጋና ተምራ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል መሆን የቻለች ወጣትም አለች፡፡ በማዕከሉ ከሚያድጉ ህፃናት በተጨማሪ ማዕከሉ ድጋፍ የሚያደርግላቸውና ከቤተሰቦቻቸው ጋር የሚኖሩ የኅብረተሰብ ክፍሎችም አሉ።

‹‹አቤኔዘር ሰፖርቲንግ ኤንድ ዴቨሎፕመንት አሶሴሽን›› ህፃናትን ከማሳደግ ባሻገር ሌሎች ግብረ ሰናይ ተግባራትንም ያከናውናል፡፡ ለአብነት ያህል በጌዴኦ እና በሐዋሳ ከተማ የሰላም መደፍረስ ችግር ባጋጠመበት እንዲሁም በኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ (COVID-19) ወቅት ያደረጋቸው ድጋፎች የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ በውጭ ከሚገኙ በጎ አድራጊዎች በሚገኝ ድጋፍ የሚንቀሳቀሰው ድርጅቱ፣ በተማሪዎች ምገባ መርሃ ግብር ላይም ንቁ ተሳትፎ ያደርጋል፤ ለአምስት ዓመታት ከ3ሺ 700 በላይ ለሚሆኑ ተማሪዎች ምገባ አድርጓል፡፡ ድርጅቱ በክልሉ ግምገማ ከተደረገባቸው መሰል ተቋማት መካከል የተሻለ አፈፃፀም ያለው እንደሆነም ተመስክሮለታል።

አቶ አርጋው በስራቸው ስላሳኩት ነገር ሲናገሩ ‹‹በሕይወት ሊኖሩ ለማይችሉና እንዲገደሉ ለተፈረደባቸው ብዙ ህፃናት ሕይወት ሰጥተናል። መፀዳጃ ቤት ውስጥ የተጣሉና ተቀብረው የነበሩ ህፃናትን አውጥተን አሳድገናል፡፡ ይህ በጣም ያስደስተናል›› ይላሉ።

አቶ አርጋው የበጎ አድራጎት ስራቸውን መለስ ብለው ሲገመግሙት ህፃናቱን ለዚህ ሁሉ ችግር የዳረጋቸውና የሁሉም ችግሮች መነሻ የሰላም እጦት እንደሆነ ተረዱ፡፡ የሰላም እጦቱ ደግሞ በግለሰብ፣ በማኅበረሰብና በአገር ደረጃ የሚገለፅ ይሆናል፡፡ ‹‹እኛ ስራ ከጀመርንበት ጊዜ ጀምሮ የችግረኞች ቁጥር ሲጨምር እንጂ ሲቀንስ አላስተዋልንም፡፡ ገንዘብ ማጣት ሁሉም ሰው ዘንድ የሚገኝ ችግር ላይሆን ይችላል፤ ሰላም ማጣት ግን ሁሉም ሰው ዘንድ የሚገኝ ችግር መሆኑን አስተዋልን። ስለዚህ የችግሩን ምንጭ መለየትና መሰረታዊ መንስዔው ላይ አተኩረን መስራት እንዳለብን ስለተገነዘብን ሰላምን በዘላቂነት ስለማስፈን ማሰብ ጀመርን›› በማለት ‹‹ግሎባል ፒስ ባንክ›› (Global Peace Bank) የተሰኘውን ሌላውን ተግባራቸውን እንዴት እንደጀመሩት ያስረዳሉ።

አቶ አርጋው ስለ ‹‹ግሎባል ፒስ ባንክ›› ጽንሰ ሃሳብ ሲገልፁ ‹‹ሰዎች ገንዘብ አዋጥተው የንግድ ባንኮችን ይመሰርታሉ። ትርፋማ ሆነውም ገንዘብ ይሰበስባሉ፡፡ ትርፋቸውን ለማስጠበቅም ባንኩን ይጠብቃሉ፡፡ ሰላምንም እንደዚህ ማድረግ ይቻላል፡፡ ሰላም ከገንዘብ በላይ ነው፡፡ እኛ ሰላምን ጋሪ፣ ገንዘብን ፈረስ አድርገናል፡፡ ሰላም በማጣታችን በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎችና በቢሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ አጥተናል፡፡ ሰላም ከሌለ የገንዘብ ባንኮች ዋስትና የላቸውም፡፡ ዋስትናቸው ዘላቂና አስተማማኝ ሰላም ነው፡፡ ስለዚህ ሰላምን ኢንቨስት ማድረግ ይገባል፡፡ ሰላም የሚገነባው ደግሞ በሰላም ሃሳብ ነው። የሰላም ባንክ ሰላምን ሊያሰፍኑ የሚችሉ ሃሳቦች የሚሰበሰቡበት የሃሳብ ባንክ ነው፡፡ የንግድ ባንኮች ውስጥ የባለአክሲዮኖች ሀብት ገንዘብ ነው፤ የሰላም ባንክ ውስጥ ደግሞ አክሲዮኑ የሰላም ሃሳብ ነው።

ሰላም በኢትዮጵያ፣ በአፍሪካ ብሎም በመላው ዓለም ሰፍኖ የማየት ርዕይ ያለው ባንኩ፣ አዲስ አበባን ጨምሮ በፌደራልና በክልል ከተሞች 13 ከፍተኛ የፖሊሲ እና 120 ማኅበረሰብ ተኮር ውይይቶችን የማዘጋጀት እንዲሁም በትምህርት ቤቶችና በመስሪያ ቤቶች የሰላም ክበባትን የማቋቋም እቅድ አለው።

የሰላም ባንክ ምስረታ ሃሳቡ በሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን ተቀባይነት አግኝቶ የእውቅና የምስክር ወረቀት አግኝቷል፤ ሃሳቡም በኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽሕፈት ቤት ተመዝግቧል፤ ከሲዳማ ክልል መንግሥትም የድጋፍ ደብዳቤዎችን አግኝቷል፡፡ ወደ ተለያዩ አካባቢዎች ተንቀሳቅሰው ሃሳቡን ለማስረዳት ባደረጉት ጥረትም የጋሞ ዞን የመጀመሪያው የባንኩ ባለአክሲዮን መሆን ችሏል።

አቶ አርጋው እንደሚሉት፣ ባንኩ ‹‹ቅድሚያ ለጎረቤት›› በሚል መርህ (Neighbor First Approach) ይመራል፡፡ ጎረቤት የሚባለው በመኖሪያ ቤት አካባቢ በቅርበት ያለው ሰው ብቻ ሳይሆን በስራ ቦታና በሌሎች እለታዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በቅርበት የሚገኘው ሰው ጭምር ማለት ነው፡፡ ከድርድር ይልቅ እርቅ የተሻለ ነው፡፡ ዘላቂ መፍትሄ የሚሆነው እርቅ ነው፤ እርቅ ደግሞ ለሰላም ዋስትና ይሆናል፡፡ የሰላም ባንክ ለሰላም ዘላቂ ዋስትና በሚሆኑ ግብዓቶች ላይ ያተኩራል።

የወደፊት እቅዳቸውን በተመለከተም ‹‹ድርጅቱ ዘላቂና ራሱን በራሱ የሚያስቀጥል እንዲሆን እንፈልጋለን›› የሚሉት አቶ አርጋው አየለ፣ ‹‹ከመንግሥት ድጋፍ ከተደረገልን፣ ከአገር ውስጥም ሆነ ከውጭ እገዛ የምናገኝበትን መንገድ አመቻችተን የበጎ አድራጎት ስራችንን ማጠናከር እንፈልጋለን›› በማለት ከመንግሥት ድጋፍ እንዲደረግላቸው በአፅንዖት ይጠይቃሉ።

ማህበራዊ

# ወጣቶች

## ባህርዳርን የስነ-ጥበብ ኮሪደር ለማድረግ እየተጋ ያለው ወጣት

ማህሌት አብዱል



**የመጀመሪያ ዲግሪውን በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ በኢኮኖሚክስ ትምህርት ዘርፍ ነው ያገኘው። ይሁንና ለጥበብ ባደረበት ትልቅ ፍቅር ምክንያት ይሰራበት ከነበረው የልማት ድርጅት በመተው ለአራት ዓመታት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ አለ የስነጥበብ እና ዲዛይን ትምህርት ክፍል በስነ ቅብ ሴሳ የመጀመሪያ ዲግሪ እና የማስተርስ ዲግሪውን ሰርቷል፡፡ ሳለፉት 11 ዓመታት በተለያየ የትምርት ተቋማት በመምህርነት ያገለገለው ይህ ወጣት ከእነዚህም መካከል ዩኒቲ ዩኒቨርሲቲ እና የተለያዩ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ካለፉት ስድስት ዓመታት ወዲህ ደግሞ በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ አርቴክቸር ትምህርት ክፍል መምህርነት እያገለገለ ሲሆን ከዚሁ ጎን ለጎንም ባህርዳር ከተማን በስነ-ጥበብ የቱሪዝም ኮሪደር ለማድረግ አልሞ በራሱ ተነሳሽነት ከፍተኛ ሥራ እየሰራ የሚገኝ ብርቱ ወጣት ነው፡፡**

**በሥዕል እና በበጎ አድራጎት ሥራዎች ለሴች ወጣቶች አርአያ የሆነውም መምህር እያዩ ገነትን የዛሬው ለወጣቶች አምዳችን እንግዳ አድርገነዋል፡፡ እንደሚከተለው ይቀርባል፡፡**

**አዲስ ዘመን፡- የእይታ ጥበብ ማለት ምን ማለት እንደሆነና በሥሩ ምን ምንን እንደሚያካትት ግለፅልንና ውይይታችንን እንጀምር?**

**መምህር እያዩ፡-** ጥበብ እንደሚታወቀው የሰው ልጅ ምድር ላይ መኖር ከጀመረ ጊዜ ጀምሮ ራሱን ለመግለፅ፣ ለመግባባት፣ ለመነጋገር እንደዚሁም በልቡና በምናቡ ያለውን ነገር ከተደራሲው ወይም ደግሞ ከሚያነበው፣ ከሚያደምጠው ጋር ለመግባባት የሚያስችል ለሰው ልጅ የተሰጠ መለኮታዊ እውቀት ነው።የሰው ልጅ ቋንቋ ከመፍጠሩ በፊት በምስል ነው ይግባባ ነበር።ስለዚህ እኔም የእይታ ጥበብ ሲባልም ጥበብ ብዙ ዘውግ ቢኖረውም ከዚያ መካከል የሚታይ፣ ታይቶም የሚተነተን፣ ትናትን፣ ዛሬንና ነገን የሚያገናኝ፣ አንድን ነገር የሚጠቁም፣ የሚሞግት ማለት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ያለህን ተሰጥኦና ሙያ በመጠቀም የተለያዩ የበጎ አድራጎት ሥራዎችን ማከናወንህ ይታወቃል፣ እስቲ ስለእነዚህ ስራዎቹ በጥቂት አብራራልን?**

**መምህር እያዩ፡-** እንዳልሽው የተለያዩ የበጎ አድራጎት ስራዎች ውስጥ ተሳትፌያለሁ።ከእነዚያ መካከል ጎልተው የሚወጡት ለምሳሌ የአርትስኩል ተማሪ በነበርኩበት ጊዜ ባህርዳር ምንምአይነት የአርት ተቋም ስለሌለ አብዛኛው ተሰጥኦ ያለው ወጣት እድሜው ሲደርስ እያዘነ ለጊዜው እጁ ላይ ባገኘው የትምህርት ዘርፍ ነው የሚገባው።በተለይም እኔ ያንን ባደረኩባቸው ጊዜያት ከባህርዳር ብዙ ልጆች ስለሚመጡ ምን የተለየ ነገር አለ? የሚል ጥያቄ ይፈጠርብኝ ነበር።ከዚያ የተነሳ ቢያንስ ተሰጥኦ ያላቸው ወጣቶች እኔ ያገኘሁትን እድል ማግኘት አለባቸው በሚል የባህርዳር ሁለገብ ሞዴል የወጣት ማዕከል በሰጠኝ ሶስት ሺ ብር ድጋፍ ብዙ ቁሳቁስ ገዝቼ ለሁለት ዓመታት 80 ወጣቶችን በክረምት አሰልጥኛለሁ። ከእነዚህም መካከል አስር የሚሆኑት አሁን ላይ አርትስኩል መግባት ችለዋል።

ሙያዬን ተጠቅሜ ህዝብን ላገለግል የምችልባቸው እድሎች ሳገኝ ወደኋላ አልልም።ያሉትን እድሎች ሁሉ በመጠቀም ወገኖችን ማገዝ ያስደስተኛል።ከዚህ ጋር ተያይዞ አንድ ምሳሌ ባነሳልሽ ወንፈል ኤድ የሚባል ድርጅት አማራ ክልል ገጠራማ እና ምንም አይነት እድል በሌላቸው አካባቢዎች ለምሳሌ ሰቆጣ አካባቢ በሚገኙና ዛፍ ስር ቁጭ ብለው ለሚማሩ ህፃናት አዳሪ ትምህርት ቤቶች ለመስራት ታስቦ እኔም በክፍያ እንዳግዛቸው ከተስማማን በኋላ ሁኔታውን ሳያው በጣም የሚያሳዝን ስለነበር እኔ ራሴ በነፃ ድጋፍ አደረግኩላቸው።የሚገርምሽ ያ ስዕል ከ40 ሺ ዶላር በላይ ተሸጦ ያንን ዓለማ ደግፏል።ይህም በህይወቴ በጣም ከተደሰትኩባቸው ጉዳዮች አንዱ ነው።

ከዚህም ባሻገር የስነ-ጥበብ የስነ ልቦና ህክምና በተመለከተ በተለይ ችልድረን ፈንድ ኦፍ ካናዳ ከሚባል ተቋም ጋር በተለያየ ቀውስ ውስጥ ያሉ ልጆችን ለአንድ ወር በሚሆን ስልጠና ህመማቸውን እንዲያወጡ፣ ስሜታቸውንና ራሳቸውን እንዲገልፁ በማድረግ የበኩሌን አስተዋፅኦ አበርክቻለሁ። ኮቪድ በተከሰተበት ወቅትም ዶክተር ዮርዳኖስ በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ የጤና ሳይንስ ኮሌጅ ጥበበ ጊዮን ሆስፒታል ውስጥ ያለውን ችግር ገለፀችልኝና እኔም ለማገዝ ተስማማሁ።ግን የተወሰነ የቀለም በጀት ብቻ ነው የተገኘው፣ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ በሆስፒታሉ በሚገኙ ሙሉውን የህፃናት ክፍልና ኮሪደር በነፃ አስውቢያለሁ።

ልጆች በተለያየ የጤና ችግር ምክንያት ወደ ሆስፒታል ሲመጡ የስነ-ልቦናዊ ድጋፍ ስለማያገኙና አብዛኛው ሆስፒታል ገፅታ ለእይታ የማይማርክ በመሆኑ የስቃይ ቦታ አድርገው እንዲያስቡ የሚያደርግ ነው።ነገር ግን ሆስፒታል የስቃይ ቦታ ሳይሆን ስቃይ የሚታከምበትና የሚድንት ቦታ ነው። ለዚህም ነው ሃሳቡ ሲቀርብልኝ ሳላንገራግር ስራ የጀመርኩት፣ ግን ደግሞ የሚሰራው በብረት ቀለም ስለሚሰራ ሽታው ከፍተኛ ችግር ፈጥሮብኝ ነበር።ሆኖም እግዚአብሔር ረድቶኝ ሰርቼ አሰርክቤያቸዋለሁ።አሁን ከገጠር የሚመጡ ሰዎች ያንን ስዕል እያዩ የሚሰጡት ግብረመልስ በጣም የሚያስደስት ነው።እንዲህ አይነትና መሰል ስራዎች በስፋት አከናውኛለሁ።

በተጨማሪም የባህርዳርን ኮሪደሮችን ለማስዋብ ከፍተኛ ጥረት አድርጊያለሁ።ባህርዳር የቱሪዝም ከተማ እንደመሆንዋ ፐፐሊክ አርት ያስፈልጋል፣ ባዶና ትልልቅ ግድግዳዎች በስነ-ጥበብ መሞላት አለባቸው በሚል የአማራ ብልጽግና ፅህፈት ቤት ግድግዳ ላይ 70 ሜትር በሶስት በሜትር በሚሆን ስፍራ ላይ ለይኩን ወንዲፍራው ከሚባል ሰዓሊ ጋር በመሆን ባህሉን በሚያጎላ መልኩ ታይምለስ የሆነ ስዕል በሞዛይክ አብረን ሰርተናል።ከዚህም ባሻገር በተለያዩ ባህላዊ ሬስቶራንቶችና ሆቴሎች ላይ ኢትዮጵያን የሚወክሉ ስራዎችን ሰርቻለሁ።በከተማዋ ባሉ ኮሪደሮች ሁሉ የአገሪቱ ታሪክ፣ ወግ እንዲታይ ሰው እየተዝናናም በሚያየው ነገር ከባህሉ ጋር እንዲገናኝ ጥረቶችን አድርጊያለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- ሥነ- ጥበብ ዘርፍ ለአገር ያለውን ጠቀሜታ በሚመለከት ማህበረሰቡ መረዳትን እንዴት ትገልፀዋለህ?**

**መምህር እያዩ፡-** በዚህ ረገድ የህብረተሰቡ ግንዛቤ አድጓል ብዬ አላምንም፣ እርግጥ ነው በመንግስት ደረጃ ለስነ- ውበት የተሻለ አረዳድ እየመጣ ነው።ግን ያ አመለካከት እያንዳንዱ ክልሎችና ከተሞች ድረስ አልወረደም። በተለይም እንደባህርዳር አይነት በታሪክም፣ በተፈጥሮም የታደለች ከተማ ውስጥ ምንም አይነት ሙዚየም ያለመኖሩ ለዘርፉ የተሰጠውን ዝቅተኛ ቦታ ያሳይሻል።በዚህ ውብና የጥበበኞች መፍለቂያ ከተማ አንድ የጥበብ ኮርነር አለመኖሩ በግሌ ያሳዝነኛል።በዚህ ከተማና ዙሪያዎቿ ባሉ ገዳማት ሃይማኖታዊ እሴታቸው እንዳለ ሆኖ ወደ ውስጥ ጠልቀሽ መጨረሻ ላይ የምታይው ግን የአባቶችን መንፈሳዊ ስዕሎች ነው።ለቱሪስቱ ያንን አሳይተሽ አሁን ደግሞ ያሉ ጠቢባን ይህንን ይሰራሉ ማለት ካልቻልሽ የትውልድ ክፍተት አለ ማለት ነው፣ ለተመልካቹም የቀደመው የስነ-ጥበብ ቅርሳችን እውነት አይመስልም።ስለዚህ እነዚህ ሁኔታዎች ዘርፉ ያለውን አገራዊ ጠቀሜታ በሚመለከት ንቃተ ህሊና አለ ለማለት አያስደፍሩም።

በግልና በተበታተነ መንገድ ሰዓሊው ወይም የጥበብ ባለሙያው ከሚጥረው ውጪ ለመደገፍ፣ የበለጠ ያንን ነገር ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ለመውሰድ፣ በተለይ የቱሪስቱን ቆይታን ለማራዘም የሚደረገው ጥረት እምብዛም ነው። እኔም በራሴ ተነሳሽነት እየሰራሁ ያለሁት አንዱ ስራ የቱሪስቱን ቆይታ የሚያራዝሙ የስነ-ጥበብ ሥራዎችን ላይ የሚያተኩር ነው። በአንድ ሰዓት ውስጥ ባህርዳርን ጥሎ ሊወጣ የሚችል ቱሪስት ምሳ የሚበላበት ቦታ ላይ እዛው እንዲቆይ የሚያደርጉ የጥበብ ስራዎችን ማየት አለበት ብዬ አምናለሁ።ለምሳሌ አንድ ጊዜ በማህበራዊ ሚዲያ የማውቀው ሰው የእኔ የጥበብ ስራዎች ለማየት ከቤልጂየም ባህርዳር ድረስ በመምጣት ስዕል ገዝቶኝ፣ የተለያዩ ቦታዎችን ጎብኝቶና አንዳንድ ባህላዊ እቃዎችንም ጭምር ገዝቶ ነው የሄደው።ይህ የሚያሳይሽ በአንድ ሰዓሊ ምክንያት አንድ ሰው ሃብት ይዞ መጥቶ እዚህ አውጥቶ መመለስ ማለት ለአገር ትልቅ ትርፍ የሚያስገኝ መሆኑን ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ከዚህ ጋር ተያይዞ የጥበብ ተሰጥኦ ያላቸውን ወጣቶች የሚያበረታታ የትምህርት ስርዓት ያለመኖሩ ለጥበቡ ያለማደግ ምክንያት እንደሆነ ይነሳል።አንተ በዚህ ሃሳብ ትስማማለህ?**

**መምህር እያዩ፡-** አዎ፣ እንግዲህ ሁሉም ነገር ከመሰረቱ ጋር ይገናኛል።በየትኛውም ሙያ የመጨረሻው ፍሬ የሚወሰነው ዘሩ ላይ ነው።ዘሩ ላይ ልክ ያልሆነ ነገር ካለ ያንን ተከትሎ ስለሚበቅል የተስተካከለ ፍሬ አንጠብቅም።በተለይም ደግሞ አንድ ሰው ዝንባሌው ባለበት ርዕሰ ጉዳይ ላይ ሲሆን ነው ውጤታማ የሚሆነው።ፈጣሪ የሰጠውን ተሰጥኦ ነው፣ ሊሰራ የሚችለውና የሰራው ነገር ደግሞ በሌሎች ሲታይ የሚስብ፣ የሚማርክ ነው።ነገር ግን ሰው ችሎታው እንኳን ቢኖረው ልቡ በሌለው ነገር ላይ ከሆነ አንድ ጊዜ ከማድረግ በዘለለ ብዙ ጊዜ ሊያደርገው አይችልም።ከዚህ የተነሳ ውጤታማ ሊሆን አይችልም።ስለሆነም ከመሰረቱ መታሰብ አለበት ብዬ አምናለሁ።ማህበረሰቡም በአብዛኛው ልጆቻው ዶክተር፣ ኢንጅነር ወይም ፓይለት እንዲሆኑለት ነው እንጂ የሚፈልገው ሰዓሊ እንዲሆን አይፈልግም።ምክንያቱም ሰዓሊ በማህበረሰቡም ሆነ በመገናኛ ብዙሃን የሚወከልበት መንገድ



መጥፎ ነገር ስለሚበዛው ነው።

አንድ ወጣት ሰዓሊ ከሆነ ሱሰኛ ይሆናል፣ ወይም ራሱን የሚገልፅበት መንገድ በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት የሌለው ይሆናል የሚል ፍራቻ ስላለ ችሎታ እንዳለው እያወቀ መቀበል አይፈልግም።ግን እውነቱን ለመናገር እንደፈረንሳይ ያሉ አገራት ሞናሊዛን የመሰለ አንድ ስዕልን ለማየት በየአመቱ 40 ሚሊዮን ሰው ወደ አገሪቱ ይሄዳል።ያ ብቻ አይደለም፣ በቆይታው ሆቴል ይይዛል፣ ለምግብ ያወጣል፣ ሌሎችን ነገሮችን ይግዛል።ያም ለአገሪቱ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ያስገኛል።ከዚህ ጋር ተያይዞ እኔም ፈረንሳይ በተካሄደ የአርት ፌስቲቫል ላይ ተካፍዬ አውቃለሁ።እኔ አገርን ወክዬ ስሄድ ብሔራዊ ባንክ ከ200 ዶላር በላይ ማቅረብ አንችልም ብሎኝ ያቀድኩትን ሁሉ መፈፀም ሳልችል ቀርቻለሁ።በወቅቱ ተቀባይነት ለማግኘት የግድ ሯጭ መሆን አለብኝ ወይ? ብዬ በጣም አዝኜ ነበር።በዚያ ዓለም አቀፍ መድረክ አገሬን አስተዋውቄ ስመጣ አበባ መስጠት ቢቀር ትንሽም ቢሆን እውቅና ያለመሰጠቱ አሳዝኖኛል።ከዚህ አንጻር ልጆችን ልክ እግር ኳስ ፕሮጀክቶች እንደሚኖሩ የስነ-ጥበብ ፕሮጀክቶች ከልጅነታቸው ጀምሮ ከቀለም ትምህርቱ ጎን ለጎን ማስተማር ፋይዳ አለው።በተጨማሪም በየከተሞቹና ገጠሩ ማሰልጠኛዎች ሊከፈቱና ማንኛውም ተሰጥኦ ያለው ወጣት ወደዚህ ኢንዱስትሪ መምጣት አለበት ብዬ አምናለሁ።ይሄ እየሰፋ ሲሄድ ለቱሪዝም እድገት የበለጠ ጠቀሜታ ይኖረዋል።ምክንያቱ ስነ-ጥበብ አለማቀፍ ቋንቋ ነው።ስለዚህ የትም አገር ያለ ሰው ሊግባባት የሚችል ነው።ስለሆነም ከኬጂ ጀምሮ በሙዚቃ፣ በስነ-ጥበብ፣ ቲያትር ነክ ነገሮች ማጠቃለያ እነሱን አቅም የሚያሳድጉ ነገሮች በፖሊሲም ደረጃ መኖር አለባቸው ብዬ ነው የማስበው።

እርግጥ ነው፣ ወላጆች ልጆቻቸው ወደ ስነ-ጥበብ ሙያ እንዲገቡ የማይፈልጉበት ምክንያት በአብዛኛው ኢኮኖሚያዊ ነው።በአብዛኛው ከባህል አንፃር በሚዲያም፣ በፊልሞችም ሰዓሊዎች የሚገልፁት ለምሳሌ አንድ ወላጅ ልጁ ልክ እንደ እጅግ የተከበሩ የዓለም ሎሬት አፈወርቅ ተክሌ ከሆነ ሰዓሊ መሆኑን ላይጠላው ይችላል።ምክንያቱም እሳቸውን በማህበረሰቡ ዘንድ የገነኑበት መንገድ በጣም ትልቅ ስለነበረ ነው።በተጨማሪም ለስዕል ሙያ መከበር ትልቅ ሚናም ስላበረከቱ በዚያ ምክንያት አብዛኛው ሰው ለእሳቸውና እንደእሳቸው ለሚሆን ሰዓሊ ክብር አለው።ግን ደግሞ ሁሉንም ባለሙያ በደምሳሳው እንደሱሰኛ የሚፈረጁበት ሁኔታ አለ።

አሁንም ድረስ በስዕል ማደግ ይቻላል ብሎ ለማሰብ የሚሰጋው ሰው ቁጥር ቀላል አይደለም። ግን ይሄ መጨረሻ መታሰብ የሚገባው ጉዳይ እንጂ የመጀመሪያ ሊታሰብ የሚገባው ምንድን ነው አቅሜ ወይም ችሎታዬ ብሎ ነው።ስነ-ጥበብ ማለት ስዕል መሳል ብቻ አይደለም፣ ለምሳሌ እኔ ስዕል ብቻ አይደለም የምሰራው፣ ጎን ለጎን ለመማሪያ ግብዓትነት የሚያገለግሉ ኢሉስትሬሽኖች እሰራለሁ።ያንን ማድረግ ስዕል ከመሳል ጋር አይጋጭም።ገቢ ማግኘት የሚያስችል ተዛማች የሆኑ ስራዎች መስራት ይቻላል። እኛም ቢሆን ይሄነው ብለን የሚብለጨለጭ ወይም የምናሳየው ሃብት ባይኖረንም በሙያችን የምንወደውን እና የምንፈልገውን ነገር ሆነን እየኖርን ነው።ስለዚህ ስነ-ጥበብ የገቢ ምንጭ አይሆንም የሚለው አስተሳሰብ ስጋት እንጂ ተጨባጭ ሁኔታን አያሳይም ለማለት እወዳለሁ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ስነበረን ቆይታ በዝግጅት ክፍሉ ሥም ከልብ አመሰግናለሁ፡፡**

**መምህር እያዩ፡-** እኔም አመሰግናለሁ፡፡

# የምድር በረከት

# የማዕድን ሀብት ጥናትና ልየታ የሚያስፈልገው ክልል

ስምስም መንግሥቱ

የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ዘንድ የሚታየው ጥፍጥፍ ወርቅ ብዙ ልፋትን አልፎ የተገኘ ነው። በዋጋቸው ውድና የሰዎች ክብር መገለጫ የሆኑ ከከበሩ የድንጋይ ማዕድናት የሚሰሩ የአንገት፣የእጅ፣ የጣት፣ የጆሮና የተለያዩ ጌጣጌጦችም በቀላሉ ከጉድጓድ ውስጥ የተገኙ አይደሉም፤ ወደ ጌጣጌጥነትም ለመቀየር የሚወስደው ጊዜና ልፋትም ብዙ ነው።

አልሚዎቹ በአንገታቸውና በጀርባቸው ላብ እንደ ውሃ እየተቆንቆረ ነው እነዚህን ማዕድናት የሚያመርቱት። በያዙት ባህላዊ መቆፈሪያ የሚምሱት ጥልቅ ጉድጓድ አፈር ተደርምሶ እንደሚጎዳቸው አያስተውሉም፤ ስራ ስራቸውን ነው የሚመለከቱት። ማዕድኑን እስኪያገኙ ድረስ ቁፋሮአቸውን ይቀጥላሉ፤ ሊደርስባቸው የሚችለው ጉዳትና ድካም ብዙም አይታሰባቸውም።

ይህን ሁሉ የሚያከናውኑት የረጋ ራስን መጠበቂያ ሳያደርጉ ነው። ማዕድኑን ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ የሚጠቀሙባት ባትሪ ብርሃን ትፈነጥቃለች ተብላ የማትገመት አነስተኛ ባትሪ ናት፤ እሷን በግንባራቸው ላይ አርገው ነው የሚጠቀሙባት። ከብዙ ልፋት በኋላ የተገኘውን የወርቅ ማዕድን አጥበው ከአፈሩ የሚለዩበትና ደቃቁን ወርቅ ሰብስበው አቅልጠው በጥፍጥፍ መልክ የሚያዘጋጁበት ዘዴም እጅግ ኋላቀር እንደሆነ ይታወቃል።

በዚህ ውስጥ ሁሉ አልፈው ለገበያ አውለው የሚያገኙት ገቢ ኑሮአቸውን የሚያሻሽልላቸው አይደለም። ከተመሳሳይ ኑሮ እያወጣቸው እንዳልሆነም ከሚያለሙበት ዘዴ ጀምሮ ያለው ሂደት ይመሰክራል። ግን ደግሞ እንደ ኢትዮጵያ ሲታይ በማዕድን ዘርፉ እነዚህ አልሚዎች ናቸው በአገር ኢኮኖሚ እድገት ላይ ሚና እየተወጡ የሚገኙት። የዘርፉ ተስፋ የተጣለባቸውም እነሱው ናቸው።

በአገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያው የአስር ዓመቱ መሪ እቅድ ከአምስት የኢኮኖሚ የትኩረት አቅጣጫዎች የማዕድን ዘርፉ አንዱ ሆኖ በእቅድ ሲያዝም የባህላዊ ማዕድን አልሚዎች ሚናም ታሳቢ ተደርጎ ነው። ምንም እንኳን በዚህ ወቅት ዘርፉን ለማዘመን በተለይም የወርቅ ማዕድን መቆፈሪያ፣ ወርቁን ከአፈሩ ለይቶ በማጠብና ወርቁንም በአንድ ጨፍልቆ ከብክነት የሚከላከል የማጠቢያ ማሽኖችን በአገር ውስጥ ማቅረብ እየተቻለ ቢሆንም፣ የማዕድን ልማቱ ሙሉ ለሙሉ ከባህላዊ የልማት ዘዴ አልተላቀቀም። በሂደት ግን የአልሚውን ድካም የሚቀንስና ብክነትንም የሚያስቀር ቴክኖሎጂ ጥቅም ላይ እየዋለ ያለበት ሁኔታ እየተስፋፋ ከመጣ ባህላዊው የማዕድን ልማት በዘመናዊው እየተተካ ይመጣል።

መንግሥት የነደፈውን አገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ አቅድ ለማሳካት ጥረት እያደረገ ባለበት በዚህ ወቅት ከማእድን ዘርፉ የሚገኘውን ምርት ለማሳደግ የባለድርሻ አካላት ትብብር ወሳኝ ነው። በዚህ ረገድም የማዕድን ልማቱ የሚከናወንባቸው ክልሎች የላቀ ድርሻ አላቸው። ለኢንዱስትሪና ለግንባታው ዘርፍ እንዲሁም ለጌጣጌጥ የሚውሉ የማዕድን አይነቶችን በጥናት ለይቶና አደራጅቶ ለኢንቨስትመንት ምቹ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። የማዕድን ልማቱ የተረጋጋ ሰላምና የተሟላ መሠረተ ልማት የሚፈልግ በመሆኑም ይህንን ሁሉ ታሳቢ ያደረገ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ተጨማሪ የቤት ሥራቸው ይሆናል።

ከባለድርሻ አካላት መካከል የሚጠቀሱት ዩኒቨርሲቲዎችም ከመማር ማስተማር ጎን ለጎን የአካባቢውን ማህበረሰብ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ለማሳደግ የሚያስችል የምርምር ሥራ ማከናወን ይኖርባቸዋል። ከዚህም በተጓዳኝ አገራዊ የምጣኔ ሀብትንም ሊያሳድጉ የሚችሉ የምርምር ውጤቶችን ለፖሊሲ አውጭዎች የማመላከት፣ ዘርፉን ለሚመራው አካል በመስጠትና የተለያዩ ድጋፎችን የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው። በቅርቡ በአማራ ክልል የሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች ከክልሉ የማእድን ልማት ቢሮ ጋር የማእድን ሀብት ለየታ ጥናት ለማካሄድ ያደረጉት ስምምነት ለእዚህ በአብነት ሊጠቀስ ይችላል።

እኛም በዚህ ረገድ የጋምቤላ ክልል ማእድን ልማት ቢሮና የጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ ይህን ኃላፊነታቸውን እንዴት እየተወጡ ስለመሆናቸው የእነዚህን አካላት



የሚመለከታቸውን ክፍሎች አነጋግረናል።

እጅግ ሞቃታማው የጋምቤላ ክልል በረሃውን የሚያስረሳ ታይቶ በማይጠገብ አረንጓዴ የተሞላ ነው። በዚህም የበረሃው ገነት የሚል ስያሜ አግኝቷል። በአሣ ሀብቱም ይጠቀሳል።የአሣ ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ በማቋቋም ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትን ለማሳደግ በአንድ ወቅት መንግሥትም ትኩረት ሰጥቶት ነበር። በክልሉ በተገነባው የአልዌሮ ግድብ ሰፊ የመስኖ ልማት ማካሄድም ይቻላል። አሁንም ቢሆን በተወሰነ መልኩም ቢሆን በግድቡ አንድ ኩባንያ የመስኖ ልማት እያካሄደ ይገኛል።

ክልሉ ከነዚህ ሀብቶች በተጨማሪ የማዕድን ሀብት ባለቤትም ስለመሆኑ ይታወቃል። በምጣኔ ሀብት እድገት ውስጥ ትልቅ ሚና ያለው የወርቅ ማዕድን ልማት በማከናወንም ተጠቃሽ ሆኗል። ከጥቂት ዓመታት ጀምሮ በልዩ ትኩረት በክልሉ ዲማ ወረዳ ውስጥ እየለማ ያለው የወርቅ ማዕድን አበርክቶው ከፍ እያለ መጥቷል። ልማቱ በስፋት የሚከናወንበት ዲማ ወረዳ ለአብነት ይጠቀስ እንጂ በተለያዩ የክልሉ አካባቢዎች ሀብቱ መኖሩን ከክልሉ ማእድን ሀብት ልማት ቢሮ የተገኘው መረጃ ያመለክታል። በክልሉ ለተለያየ ግብአት የሚውሉ ማዕድኖች መኖራቸውን በተለያየ ጊዜ የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያመለክቱም የጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ አስታውቋል።

በክልሉ እየተከናወነ ስላለው የማዕድን ልማትና ከወርቅ ማዕድን በተጨማሪ ሌሎች የማዕድን ሀብቶችን ጥቅም ላይ በማዋል ረገድ ስላለው እንቅስቃሴ የጋምቤላ ክልል ማእድን ሀብት ልማት ቢሮ ዋና የሥራ ሂደት አቶ ሙድ ሎንግ እንደገለጹት፤ በክልሉ በርካታ ማእድናት ቢኖሩም፣ ለጊዜው በትኩረት እየተሰራበት ያለው የወርቅ ማዕድንና ለግንባታ ግብአትነት የሚውሉት አሸዋና ድንጋይ ናቸው።

በክልሉ በሚገኙ ባሮ፣ አልዌሮና ኢሉ ወንዞች አካባቢ ከፍተኛ የአሸዋ ክምችት ይገኛል። በባሮ ወንዝ ደግሞ የክምችት መጠኑ ከፍተኛ ነው። እንደ ሴራሚክ ያሉ የግንባታ ማጠናቀቂያ ማእድናት፣ ግራናይትን የመሳሰሉ ማእድናት ከክልሉ ዋና ከተማ ቅርብ ርቀት ላይ ይገኛሉ።

እነዚህን ማእድናት ለማልማት አንድ ባለሀብት ባለፈው ዓመት ፍቃድ ወስዶ በእንቅስቃሴ ላይ ይገኛል። ባለሀብቱ ማዕድኑ ስለመኖሩ በጥናት ቢያረጋግጥም እስከ አሁን ግን ስራውን አልጀመረም። ባለሀብቱ ወደ ሥራ ላለመግባቱ በምክንያትነት የሚያነሳው ለሥራው የሚያስፈልገው መሳሪያ ከውጭ የሚመጣ ነው። መሳሪያውን ለማስገባት ገንዘብ ያስፈልጋል። ለዚህም ባለሀብቱ ከባንክ ብድር እንደሚጠብቅ መግለጹን ነው አቶ ሙድ ያስረዱት።

የድንጋይ ከሰል መጀንግ ቤሄረሰብ አካባቢ እንደሚገኝና ሌሎችም የማዕድን አይነቶች በክልሉ እንደሚኖሩ ከመገመቱ ውጭ በጥናት ተለይቶና ተደራጅቶ የተቀመጠ መረጃ ቢሮው ለጊዜው እንደሌለውም ገልጸዋል።

ወርቅን ጨምሮ ውስን የሆኑት የክልሉ ማዕድን ሀብቶችም መኖራቸው ታውቆ ወደ ልማቱ የተገባው በተለይም የወርቅ ማዕድኑ እየለማ ያለው በኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ ኢንስቲትዩት በተደረገ ጥናት ተለይቶ እንደሆነ አቶ ሙድ ይጠቅሳሉ።

እርሳቸው እንዳሉት፤ በክልሉ አቅም በጥናት የተደገፈ የሀብት ልየታ ለማከናወን በሥነምድር (ጂኦሎጂ) ቋንቋ ፒር ማቴሪያል ወይንም ቴክኖሎጂ እንዲሁም የናሙና ፍተሻ የሚከናወንበት ቤተሙከራ (ላቦራቶሪ) እና የገንዘብ አቅም ያስፈልጋል።

ማዕድን ሚኒስቴር በየክልሉ የሚገኙ የትምህርት ተቋማት (ዩኒቨርሲቲዎች/ በዘርፉ ላይ ጥናት መሥራት እንዳለባቸውና ቢሮዎችም ከተቋማቱ/ከዩኒቨርሲቲዎች/ ጋር እንዲሰሩ አቅጣጫ አስቀምጧል። ይህ አሰራር ክልሎች በራሳቸው አቅም እንዲንቀሳቀሱ እድል ይፈጥራል። አንዳንድ ክልሎችም ወደ ሥራ በመግባት ሀብታቸውን የመለየት ሥራ እየሰሩ እንደሆነ ይታወቃል።

በጋምቤላ ክልል ተጨባጭ ሁኔታ ግን በክልሉ የሚገኘው ጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ የጂኦሎጂ የትምህርት ክፍል ባለመክፈቱ ምክንያት በጋራ ለመሥራት አልተቻለም። አቶ ሙድ እነዚህ ችግሮች እንደሚፈቱ ተስፋ አላቸው። የክልሉ ተወላጆች የአካባቢውን ነባራዊ ሁኔታ በማስገንዘብና ትኩረት እንዲያገኝ ጥረት እንደሚያደርጉም እምነታቸው ነው። ከማእድን ሚኒስቴር ጋር ያለው ግንኙነትም ቀደም ካሉት ዓመታት የተሻለ እንደሆነ ነው የገለጹት።

የአካባቢውን የማዕድን ሀብት በጥናት ለይቶ ለሚመለከተው ክፍል በማቅረብና ከክልሉ ማዕድን ሀብት ልማት ቢሮ ጋር በጋራ በመሥራት ረገድ ጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ እያበረከተ ስላለው አስተዋጽኦ የዩኒቨርሲቲውን ፕሬዚደንት ዶክተር ኡጁሉ ኡኮክኡኩሙ ጠይቀናቸው በሰጡን ምላሽ እንዳሉት፤ ዩኒቨርሲቲው ከተቋቋመ ስምንት ነው።

ዩኒቨርሲቲው በአሁኑ ወቅት በማዕድን ዘርፍ ተማሪዎችን ተቀብሎ ለማስተማርም ሆነ ተመራማሪዎችን ለማፍራት የሚያስችል ዝግጅቱን አጠናቅቆ ወደ ሥራ ለመግባት የወራት እድሜ ነው የቀረው ሲሉ ፕሬዚዳንቱ ይናገራሉ።

ፕሬዚዳንቱ እንዳሉት፤ ዩኒቨርሲቲው በማዕድን ዘርፉ የሚጠበቅበትን ተልእኮ የሚወጣው በዘርፉ የትምህርት ክፍል ካደራጀ በኋላ ነው። ዩኒቨርሲቲው በጥናት የተጠናከረ ሥራ ለመሥራት ማዕድንን ጨምሮ ግብርና፣ ቱሪዝም፣ የተፈጥሮ ሀብት የትኩረት አቅጣጫዎች ናቸው። በዚህ በጀት ዓመት በማዕድን ዘርፉ ሰፊ ሥራዎች ይሰራሉ።

በዩኒቨርሲቲው በኩል የጥናት ሥራው ገና ቢሆንም፣ ከዚህ ቀደም በተለያየ መንገድ በተደረጉ ጥናቶች በጋምቤላ ክልል የወርቅ ማዕድን ልማት በዲማ ወረዳ ብቻ ሳይሆን፣ አኝዋክ ዞን፣አቦቦ፣ ጋምቤላ ወረዳ፣ መጃን ዞን በተወሰኑ አካባቢዎች እንዲሁም የከበሩ የድንጋይ ማዕድናት ይገኛሉ።

እንደ ክልል ብቻ ሳይሆን፣ እንደ አገር ነዳጅን ጨምሮ እምቅ የሆነ የምድር በረከት ሀብት እንዳለ የተናገሩት ፕሬዚዳንቱ፣ በሚፈለገው ልክ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም እንዳልተገኘበት ተናግረዋል። ማእድን ዘርፍ የተማረ የሰው ኃይል ከማፍራት ጀምሮ ዘርፉን ወደላቀ ደረጃ ለማድረስ የትምህርት ተቋማት ድርሻ ከፍ ያለ መሆን እንዳለበት ፕሬዚዳንቱ ዶክተር ኡጁሉ ያምናሉ። እርሳቸውም በግላቸው የሚችሉትን በማድረግ ኃላፊነታቸውን ለመወጣት ዝግጁ መሆናቸውን ነው የገለጹት።

ሁሉም የየድርሻውን ከተወጣ በዘርፉ ውጤት ማስመዝገብ እንደሚቻልም ተናግረዋል።የማዕድን ልማቱ ከሚፈልገው ሰላምና የተረጋጋ አካባቢ ከመፍጠር እንዲሁም መሠረተ ልማትን ከማሟላት አኳያም ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገባ እንደሆነ ነው የገለጹት። የአካባቢውን ሰላምን በመጠበቅ ለልማቱ ምቹ እንዲሆን ከማድረግ አንጻርም ዩኒቨርሲቲው ከማህበረሰቡ ጋር እንደሚሰራ አስታውቀዋል።

በጋምቤላ ክልል ያለውን የማዕድን ልማትና የግብይት ሂደቱን በማዘመን ሀብቱን በአግባቡ ጥቅም ላይ ለማዋል አመራሩ በቁርጠኝነት ሊሰራ እንደሚገባ የማዕድን ሚኒስትር ኢንጂነር ታከለ ኡማ ከሁለት ዓመት በፊት በክልሉ ተገኝተው ከሥራ ኃላፊዎችና ባለድርሻ አካላት ጋር ዘርፉ በሚጠናከርበት ሁኔታ ላይ ምክክር ባደረጉበት ወቅት ማስገንዘባቸውን የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት መዘገቡ ይታወሳል። ሚኒስትሩ በወቅቱም ከግብርናው ቀጥሎ ኢኮኖሚውን እየደገፈ ያለው የማዕድኑ ዘርፍ እንደሆነ መግለጻቸው በዘገባው ተመልክቷል። ለዘርፉ ማነቆ የሆኑ የአሰራርና የህግ ማዕቀፎችን ጭምር በማሻሻል ረገድ አመራሩ በቁርጠኝነት ሊሰራ እንደሚገባም አስገንዝበው ነበር። በተለይም የወርቅ ማዕድን ልማትና የግብይት ሂደቱን በማዘመን ሀብቱን ለክልሉ ብሎም ለአገር ኢኮኖሚ ግንባታ ለማዋል አመራሩ ለዘርፉ መጠናከር በትኩረት መስራት እንዳለበትም ጠቁመዋል።

ሚኒስትሩ በወቅቱ እንዳሉት፤ በሁሉም አካባቢዎች ጥናቶች እንደሚያሳዩት አብዛኛው የወርቅ ማዕድን በብር በመቀየር ለማስቀመጥ በሚንቀሳቀሱ የኢኮኖሚ አሻጥረኞች ምክንያት አብዛኛው የወርቅ ምርት ወደ ባንክ እየገባ አይደለም። ፈቃድ በተሰጣቸው የወርቅ አዘዋዋሪዎች አስፈላጊውን ክትትልና ጥናት በማካሄድ እርምጃ መውሰድ እንደሚያስፈልግም ገልጸዋል። በጋምቤላ ክልል ያለውን የወርቅ ሀብት የአመራረትና ግብይት ሰንሰለት ለማዘመን ሚኒስቴሩ አስፈለጊውን ድጋፍ ለማድረግ ዝግጁ መሆኑንም አስታውቀዋል።

በወቅቱም የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር አቶ ኡሞድ ኡጁሉ፤ በክልሉ ሰፊ የወርቅ ሀብት ቢኖርም በተፈለገው መጠን ለምቶ ለክልሉ ብሎም ለአገር ጥቅም አለማዋሉን አስታውቀዋል። ሀብቱን ዘመናዊ በሆነ መልኩ በማልማት ለአገር የኢኮኖሚ ግንባታ ለማዋል በተለይም የፌደራሉ መንግስት የቴክኖሎጂና የሙያዊ ድጋፍ ሊጠናከር ይገባል ማለታቸው ይታወሳል።

በተጨማሪም በክልሉ ሁሉም አካባቢዎች የፋይናንስ ተቋማት ተደራሽ ካለመሆናቸው ጋር ተያይዞ በግብይት ሂደቱም ሆነ በሌሎች የመንግስት መደበኛ ስራዎች እንቅፋት መፈጠሩን አስታውቀው ነበር። በክልሉ በሚገኙ የዞንና ወረዳ ከተሞች ባንኮች ተደራሽ የሚሆኑበት አሰራር ሊዘረጋ እንደሚገባም መናገራቸውን በዘገባው ተጠቅሷል።

በክልሉ መንግስት የቀረቡት ጥያቄዎች ተገቢ መሆናቸውንና የአካባቢውን ተጨባጭ ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት ተጨማሪ የባንክ ቅርንጫፎችን ለመክፈት እየተሰራ እንደሆነም የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ ደረጀ ፋፋን ዋቢ አድርጎ በወቅቱ የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ዘግቧል። ክልሉ በ2013 በጀት አመት ማጠናቀቂያ ከ1 ሺህ 213 ኪሎ ግራም በላይ ወርቅ ለብሄራዊ ባንክ ገቢ ማድረጉንም አመልክቷል።

ክልሉ በራሱ አቅም የሚያደርገው ጥረት እንዳለ ሆኖ፣ ከክልሉ የሚገኘው የወርቅና የመሳሰለው ሀብት የአገርም ጭምር እንደመሆኑ የፌዴራል መንግስት ለወርቅ ልማቱ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ይኖርበታል።

በክልሉ ህገወጥ የወርቅ ዝውውርን ለመቆጣጠር እየተሰራ ነው። ይህን ተከትሎም ከክልሉ ወደ ብሄራዊ ባንክ የሚገባው የወርቅ መጠን ጨምሯል። በልማቱም በኩል ተመሳሳይ ርብርብ ማድረግ ይገባል። የፌዴራል መንግስት፣ የፋይናንስ ተቋማት፣ ባለሀብቶች በክልሉ ያለውን ወርቅ በማልማት አምራቾቹም የክልሉ ህዝብም አገርም ይበልጥ ተጠቃሚ እንዲሆኑ መስራት ይጠበቅባቸዋል።

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## እሺ ይበልጣል ከሺ..

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

‹እማ! አልኳት ወዳለችበት ራመድ ብዬ። እማ ነው የምላት..ተሳስቼ በስሟ ጠርቻት አላውቅም። እንዲህ እንደ አሁኑ እንድታስቸግረኝ ፊቷ ቆሜ አውቃለሁ።

‹ወዬ ጌታዬ! አለችኝ..ፊቷን በትንሽ ፈገግታ ሞልታ። በእሷ አፍ ጌታዬ ስባል ነፍሴ በደስታ በልቤ ውስጥ ትሟሟለች። እያየኋት ተጠጋኋት ጠዋት ስለሆነ ፊቷ ላይ የማያልቅ ውበት አለ..እኔ ብቻ የማየው፣ ለእኔ ብቻ የተሰጠ።

አጠገቧ ደርሼ ቆምኩ..እጄን ወደ ጉንጩዋ ልኬ ዳሰስኩት። በጉንጮቿ መጫወት እወዳለሁ..አጠገቤ ስትሆን ሁሌ በጉንጩዋ ነው የምጫወተው። እጆቿን ወደለበስኩት ሸሚዝና ኮት ልካ ታስተካክልልኝ ጀመር።

‹ስመጣ ምን ላምጣልሽ? አልኳት በናፈቀ ቃና ድምጼን ዝግ አድርጌ። ዓለም ላይ የማይቻል ነገር እንድትጠይቀኝ በመመኘት። ሰሞኑን ወደ ፓሪስ እበራለሁ..ከሀሳቦቼ ሁሉ ትልቁ ከጉዞዬ መልስ እሷን ማስደሰት ነው።

‹አንተ ብቻ ናልኝ..› አለችኝ አይኗን አይኔ ላይ እጆቿን ኮትና ሸሚዜ ላይ ጥላ። ብዙ ጊዜ እንድታዘኝ፣ እንድታስቸግረኝ ፊቷ ቆሜ አውቃለሁ። ብዙ ጊዜ እንድታንገላታኝ ራሴን አዘገጅቼላት አውቃለሁ ግን ለኔ ስትለፋ ነው የማገኛት። ሁሌ ሳይገባኝ እንዳገኘኋት ሳይገባኝ የኔ እንደሆነች ነው የሚሰማኝ።

ነፍሷ ትሁት ናት..በኔ መኖር የምትኖር እንዲህም ናት፡ ምንም ነገር ልጠይቃት እሺ ነው የምትለኝ። ከአፏ እንቢ የሚል ቃል ሰምቼ አላውቅም። ብዙ ጊዜ ይሄን እሺ አትለኝም ብዬ ሰግቼ ስጠይቃት እሺ ትለኛለች። ነፍሷ ነውር የላትም.. ሴትነቷን አንድ ሳታስቀር ተቸግሮላት ለማያውቅ አንድ ወንድ ሰጥታለች። እኔ እኮ አልመጥናትም..እንዴት እጄ እንደገባች እሱ ይወቀው። መጀመሪያ ቀን ሳያት ከዛም እንዳናግራት የገፋፋኝ አምላክ እሷን ሰጥቶኝ ዳግም ላይዋሃደኝ ጥሎኝ የሄደ ይመስለኛል። በእሷ ሁሉን እንዳገኝ አድርጎ።

ብዙ ናት..አንሳና ጎድላ አይቻት አላውቅም። ልደርስባት ስሮጥ በእጥፍ በልጣኝ አገኛታለሁ። የነፍሷን ቦታ አልደረስኩበት። ሰው በዛ ልክ ለሌሎች ሲኖር፣ ለሌሎች ሲቆም እሷን ነው ያየሁት። እንደ ሚስትና እንደ እናት ናት.. እንደ ጓደኛና እንደ እህትም።

‹እማ የሆነ ነገር ላስቸግርሽ ነበር?

‹እሺ..

‹ቀዩን ቀሚስሽን ስላልወደድኩት ቢጫውን አድርጊ›

‹እሺ..

‹ብር ጨርሻለው የሆነ ገንዘብ አስገቢልኝ..

‹እሺ..

‹ዛሬ ደክሞኛል የራት ቀጠሯችንን ሰርዤዋለሁ..

‹እሺ..

እንዲህ ናት..በእሺ ተሞልታ በእሺ የምትፈስ..የጽድቅ ውቅያኖስ። ለእኔ የሚሆን ብዙ የመቸገር ጊዜ አላት። የሆነችልኝ መሆን ከሆንኩላት መሆን ጋር ባህርና ኩሬ ነው።

ማታ በእቅፏ እሞቃለሁ..በሴትነቷ ረካለሁ..ነፍሴ መቼም የማትደግመው በረከቷ ከእሷ ሴትነት ውስጥ ነው። እንደ እሷ መሆን እፈልጋለሁ፣ እንደ እሷ መታዘዝ ያምረኛል። ልታዘዛት ፊቷ ስቆም ልትታዘዘኝ ፊቴ ስትቆም አገኛታለሁ።

መቼ ይሆን የምታስቸግረኝ እላለሁ። መቼ ይሆን የማይቻል ነገር አድርግልኝ ብላ የምታስቸግረኝ እላለሁ። ለእሷ ለመቸገር ሁልጊዜም እንደተዘጋጀሁ ነው ግን አስቸግራኝ አታውቅም። ብዙ ጊዜ እንድታስቸግረኝ፣ የማይቻለውን አድርግልኝ እንድትለኝ ፊቷ በይሁንታ ቆሜ አውቃለሁ። ግን አታስቸግረኝም..ደስታዋ ለእኔ በመቸገር ውስጥ ነው። ደስታዋ ለእኔ በመልፋት ውስጥ ነው። ደስታዋ ለእኔ ሚስት ሆኖ በመቆም ውስጥ ነው።

እግዜር እኔ እንዳመሰገንኩት በወንድ አፍ ተመስግኖ የሚያውቅ አይመስለኝም። ባየኋት ቁጥር ወደ ሰማይ አንጋጥጣለሁ። እጆቼን ዘርግቼ፣ አይኖቼን አቅንቼ፣ በጽሞናና በእንጉርጉሮ፣ በለሆሳስና በሹክሹኩታ ጌታዬን ተመስጌን ብዬው አውቃለሁ። ማመስገኛዬ ናት..አሜን ማያዬ። በእሷ ብዙ ሳቅን ስቁአለሁ..

ትላንት ማታ አንድ ነገር እያሰብኩ ነበር እንቅልፍ የወሰደኝ። ጠዋት..በጣም ጠዋት እሷን የሰጠኝን ጌታ እያመሰገንኩ ሳትቀድመኝ ልቀድማት ከእንቅልፌ ነቅቼ ወደ ማዕድ ቤት ገባሁ..የመጀመሪያውን ቁርስ ሰርቼ ላበላት። ግን እንዳሰብኩት የሆነ ምንም የለኝም..ከእኔም በፊት፣ ከሰራተኞቻችንም በፊት ነቅታ ቁርስ ስትሰራልኝ አገኘኋት። ማድረግ የምችለው ሁለት ነገር ነበር ከኋላ ሄጄ እቅፍ አደረኳት።

አልቀድማትም..ደርሼባት አላውቅም ሁሌ ከኋላዋ ነኝ።

አንድ ቀን ፊቷ ቆምኩ..ፊቷ ቆሜ ጉንጮቿን አለመንካት አልቻልምና ነካኋት። እሷም እኔን ብቻ በምታይበት የፍቅር አይን እያየችኝ ‹ምነው ጌታዬ? አለችኝ።

ፍቅሯ ማብቂያ የለውም ጌታዬም ትለኛለች። እሷ ፊት ሁልጊዜም አዲስ ነኝ። በሴትነቷ ሕይወቴን አጣፈጠችልኝ..። እንዲህ እንደ አሁኑ በአዲስነት ፊቷ ስቆም ‹ሴት የሕይወት ጨው ናት..በወንድነት ውስጥ ጠብ ተደርጋ የምትጥም፡› እላለሁ..በውስጤ።

‹እማ! አልኳት

‹ወዬ ጌታዬ! አለችኝ

‹ዛሬ አንቺን የማገለግልበት ቀን እንዲሆን እፈልጋለሁ..› አልኳት።

‹እሺ..› አለችኝ።

‹ከምን ልጀምር? አልኳት..ውስጤ ከምን እንደም ትጀምር ሳታውቅ ነው ላገልግልሽ ያልከው? አለኝ።

‹እቀፈኝ› አለችኝ።

አቀፍኳት..

‹ሌላስ? አልኩኝ

‹እቀፈኝ› ስትል ደገመችልኝ።

ግራ ተጋባሁ ..አቅፌያት እቀፈኝ ማለቷ

ሁለት እጆቼን ጀርባዋ ላይ አነባብሬ ወደ ደረቴ ለጠፍኳት። ደረቴን ሰርስራ ወደ ነፍሴ እንድትገባ..

‹ሌላስ? አልኩ..ምን ትለኝ ይሆን እያልኩ።

‹ሳመኝ፣ እንደምታፈቅረኝ ንገረኝ› አለችኝ።

የተባልኩትን አደረኩ...ነፍሷ ደረቴ ላይ ስትቀልጥ ታወቀኝ። በወንድነቴ ሄርታሌ ላይ ሴትነቷ ሲቀልጠ ተሰማኝ። አስራ ሁለት አመት በትዳር ስንቆይ እንደዛሬ አስደስቻት የማውቅ አይመስለኝም። ሁሌ የምስማት አልጋ ላይ ስንወጣ ነው። የሆነ ነገር ተጋባብኝ..የሞቀ ነፍስ፣ የሞቀ ሴትነት ወደ ወንድነቴ ሰረገ።

‹ሚስትህ ምን እንደሚያስደስታት ካወክና ያን ነገር ካደረክላት አገልግለህታል ማለት ነው› አለችኝ።

ዝምታ ሰፈረብኝ..እስከ ዛሬ ምንም ሳልሆን እንደኖርኩ ታሰበኝ።

‹ሴት ልጅ ከታቀፈችና ከተሳመች እንደምትፈቀርም ከተነገራት በቂዋ ነው። አንዳንድ ወንዶች ይሄን አያውቁም። የሴትን ነፍስ ለማስደሰት ብዙ ይለፋሉ። ብዙ ሳይለፉ በትንሽ ነገር እንደሚባርኩን የሚያውቁ ጥቂት ወንዶች ናቸው።

እስከዛሬ ባስቸገረችኝ፣ የማይቻል ነገር በጠየቀችኝ ስል ማሰቤ ተራ ሆኖ ታየኝ። በተለይ እሷ እያገለገለችኝ ያለው በትንሽና በምንም በማይተካ ነገር እንደሆነ ሳውቅ እሷን ለማስደሰት ተራራ ለመውጣት ማሰቤ ስህተት እንደሆነ ተገለጠልኝ። ተበለጥኩ..በለጠችኝ..

ደረቴ ላይ ሆና ቆየች..የምትፈልገው ደስታ፣ ያልሰጠኋት እውነት ያ እንደሆነ ገባኝ። ጀርባዋ ላይ የተጠመጠመ አንድ እጄን አንስቼ ወደ አናቷ ሰደድኩት..ወደ ጸጉሯ ስር ገብቼ ዳበስኳት። ደረቴ ላይ ያንቀላፋች እስኪመስለኝ ድረስ ትንፋሸዋን ውጣ ጸጥ አለች። አረካኋት..። በደስታ ነፍሷን ገደልኳት። ወዲያው ትኩስ ትንፋሽ ደረቴን ይፈጀኝ ገባ.. ነፍስ ዘራች ስል አሰብኩ። ከእንግዲህ ተራራ ሳልወጣ እያቀፍኩና እየሳምኩ፣ እየዳበስኩና ፍቅሬን እየነገርኩ ሚስቴ ላደርጋት ለራሴ ቃል ገባሁ።

ከደረቴ ላይ ቀና ብላ አስተዋለችኝ። ቀይ ፊቷ አቅላልቷል። ያላባራ..ያልበረደ የደስታ እንፋሎት ይንቀለቀልበታል። ዝግ ብላ እንዲህ አለችኝ ‹ይሄኛውን አንተን ነው የምፈልገው..

እንደዛሬ ተዐምር ሰምቼ የማውቅ አይመስለኝም። ተጣድፌ...ተንደርድሬ ‹እሺ› አልኳት..። ተጋባችብኝ..እንደ እሷ መሆንና ማሰብ ጀመርኩ።

‹መታዘዝ ንጉስ ያደርጋል› ስትል ለሌላ የፍቅር ጨዋታ ወደ መኝታ ክፍላችን አመራን።

# ዓለም አቀፍ

## የኮሮና ቫይረስን የመራባት ሂደት የሚገታው አዲስ መድሃኒት - «ዲ ኤፍ ኮቭ 01»

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ከ6 ነጥብ 6 ሚሊየን በላይ ሰዎችን የገደለው የኮቪድ 19 ወረርሽኝ አሁንም የዓለማችን አሳሳቢው ጉዳይ ሆኗል። በሽታው ዳግም የስርጭት አድማሱን በማስፋቱም ዓለም ከሁለት አመት በፊት ወደነበረችበት ትመለሳለች የሚል ጥርጣሬን እያስከተለ ነው። ለቫይረሱ መከላከያ የተሰጡ ክትባቶችና ከዚያም በኋላ የተሰራጩ መድሃኒቶች ውጤታማነትም ማጠያየቁን ቀጥሏል።

የሰውነትን የበሽታ መከላከል አቅም ማሳደግ ላይ ያተኮሩ (አንቲቦዲ) መድሃኒቶች ኮቪድ 19ኝን የመከላከል አቅማቸው በተዳከመበት ጊዜ በአሜሪካ ተመራማሪዎች አዲስ መድሃኒት ይፋ ተደርጓል።

የዳና ፋርበር የካንሰር ኢንስቲትዩት ተመራማሪዎች ያስተዋወቁት መድሃኒት “ዲ ኤፍ ኮቭ 01” ይሰኛል። ስለ አዲሱ የኮሮና መድሃኒት ከተመራማሪዎቹ ውስጥ አንዱ የሆኑትን ዶክተር ጎርዳን ፍሪማን አል አይን ኒውስ ጠይቋል።

የሃርቫርድ ዩኒቨርሲቲ መምህሩና የጥናቱ መሪ ዶክተር ፍሪማን እንደገለጹት፥ አዲሱ የኮቪድ መድሃኒት የሰውነትን የበሽታ መከላከል አቅም የሚያሳድግ ሳይሆን የቫይረሱን መስፋፋት የሚገታ ነው።

የኮቪድ 19 ቫይረስ “ኤ ሲ ኢ 2” ከተሰኘው ሞሎኪዩል ማምለጥ አይችልም፥ ሞሎኪዩሉ ወደ ቫይረሱ ሲገባም የቫይረሱ የሕይወት ኡደት ይገታል ነው የሚሉት ተማራማሪው። ቫይረሱ የደቂቅ ህዋሳት ላይ የሚያደርሰውን ጉዳትም እንደሚያስቀም ያብራራሉ።

መድሃኒቱ በየጊዜው የሚፈጠሩ የኮቪድ 19 ዝርያዎች ለማጥፋት እንደሚያግዝ መረጋገጡንም ነው ዶክተር ጎርደን ፍሪማን ለአል አይን ኒውስ የተናገሩት። “ዲ ኤፍ ኮቭ 01” በቫይረሱ የተያዙ ሰዎችን ለማከም ይውላል ተብሏል።

መድሃኒቱ ወረርሽኙን አስቀድሞ ለመከላከልም ትልቅ ድርሻ እንደሚኖረው የዳና የካንሰር ኢንስቲትዩት የምርምር



ቡድን መሪው ይናገራሉ። የደም ግፊትን ጨምሮ ሌሎች ተያያዥ የጎንዮሽ ጉዳቶች እንደሌሉትም ነው የጠቆሙት።

በኮሮና በተያዙ እንስሳት ላይ ተሞክሮ ውጤታማ መሆኑ የተረጋገጠው አዲስ መድሃኒት በቀጣይ በሰዎች ላይ ይሞከራል ተብሏል። መድሃኒቱ በፈረንጆቹ 2023 ሙከራው ተጠናቆም ለገበያ እንደሚውልም ይጠበቃል።

## ደቡብ ሱዳን የሰላም አስከባሪ ጦር ወደ ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ ላከች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የደቡብ ሱዳን ፕሬዝዳንት ሳልቫ ኪር በጎረቤት ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ የሚሰማሩትን ከ700 በላይ የሰላም አስከባሪ ኃይሎችን ሸኝተዋል።

ሳልቫ ኪር ወታደሮቹ በተልዕኮው እንዲጸኑ፣ ስነ-ምግባር እንዲጠብቁ እና ከወንጀል ድርጊቶች እንዲርቁ ማሳሰባቸውን ሲ.ጂ.ቲ.ኤን ዘግቧል።

ፕሬዝዳንት ሳልቫ ኪር ወታደሮቻቸውን "ስነ-ምግባር እንድትጠብቁ እፈልጋለሁ፤ ወደ ሌላ ሀገር ሰላም ማስከበር ተልዕኮ ሄደው ችግር የሚፈጥሩ ኃይሎች አሉ፤ ሴቶችንና ልጃገረዶችን ይደፍራሉ፤ እናንተ አታድርጉ” ብለዋል።

“ከሰላማዊ ሰዎች ምንም ነገር አትውሰዱ፤ በምትኩ የዜጎችን ሕይወት ከአደጋ ጠብቁ” ሲሉ



ፕሬዝዳንት ኪር በደቡብ ሱዳን ዋና ከተማ ጁባ ለሚገኘው የቀጣናው ኃይል ተናግረዋል።

ደቡብ ሱዳን በኮንጎ ምሥራቃዊ ክፍል የሚገኘውን ኤም-23 አማጺን ለመዋጋት በምስራቅ አፍሪካ ማህበረሰብ ክልላዊ ኃይል የተመደበውን ከ700 በላይ “ጠንካራ ኃይሎችን” የያዘ ወታደራዊ ቡድን ልካለች።

በተልዕኮው የሀገሪቱን መልካም ገጽታ ለማምጣት ለሰላም አስከባሪ ኃይሉ ስርዓት እንዲያሰፍን ፕሬዝዳንት ኪር ጠይቀዋል።

የሀገሪቱ የመከላከያ እና የአርበኞች ጉዳይ ሚንስትር አንጀሊና ቴኒ ሀገሪቱ ለቀጣናው ሰላምና መረጋጋት እንዲሁም ለዓለም አቀፍ ሰላም የበኩሏን አስተዋጽኦ ለማበርከት የቀጣናው ሰላም አስከባሪ ኃይል አባል በመሆኗ ኩራት ይሰማታል ብለዋል።

ኃይሉ ወዲያውኑ ወደ ኮንጎ እንደሚላክና በጎማ እንደሚሰፍር ተገልጿል።ቡብ ሱዳን እስካሁን ሰላም አስከባሪ ኃይሏን ወደ ኮንጎ የላከች ብቸኛዋ አገር ነች ተብሏል። ከመጋቢት መጨረሻ ጀምሮ ኤም-23 በዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ሰሜን ምስራቅ ክፍል ጥቃቱን ማጠናከሩ ተነግሯል።

# የመማርያ መጽሐፍት በበቂ ሁኔታ ባለመሟላቱ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

መሆናቸውን አቶ አሳዬ ጠቁመው፤ መፅሐፎቹ ከሶስት እስከ አምስት ምዕራፍ ብቻ የያዙ መሆናቸውንም ተናግረዋል። የደረሷቸው መጽሐፍትም ቢሆኑ የይዘትና የምዕራፍ መዘበራረቅ እንዳለባቸው አቶ አሳዬ አስታውቀዋል።

ስማቸው እንዲጠቀስ ያልፈለጉ የምኒልክ አጸደ ሕጻናትና መጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህር በበኩላቸው፤ የትምህርት ዘመኑን በአዲሱ የትምህርት ፍኖተ-ካርታ መሰረት እንድናስተምር እየተደረገ ነው። ይሁንና የአዲሱ የትምህርት ፍኖተ-ካርታ መጽሐፍት አልደረሱንም ብለዋል።

በሞጁል መልኩ የደረሷቸው የሒሳብና የተወሰኑ ትምህርቶች መጽሐፍት ክፍሎች በሶስትና በአምስት ምዕራፎች ብቻ የተገደቡ መሆናቸውን የተናገሩት መምህሩ፤ ቀሪው የመጽሐፎቹ ክፍሎች መቼ እንደሚደርሳቸው የሚያውቁት ነገር እንደሌለም ገልጸዋል።

በአሁኑ ወቅት ተማሪዎች ከመምህራን ብቻ የሚሰጠውን የመጽሐፎቹን ይዘቶች ላይ ጥገኛ ሆነዋል። በዚህ የተነሳ ትምህርቶቹን ከማስረዳት ባለፈ የትምህርቱን ሃሳቦች በሰሌዳ ላይ በመጻፍ ተጠምደን እንውላለን። ይህ በመሆኑም ለተማሪዎች የምናስረዳበት ጊዜ እያጠረን ነው ብለዋል።

መምህራኑ አክለውም፤ የምናስተምረው የስራ ጉዳይ ሆኖብን እንጂ የመማር ማስተማር ሂደቱ ያለመጽሐፍት መሆኑ አሰልቺ ነው ሲሉ ለኢትዮጵያ ፕሬሰ ድርጀት ተናግረዋል።

የመጽሐፍቱ በወቅቱ አለመድረስ ከመምህራንና ተማሪዎች ባለፈ የወላጆችም የዘወትር ጥያቄም ሆኗል፤ በዚህም የወላጆችን ጥያቄ መመለስ አልተቻለም ሲሉ መምህራኑ ጠቁመዋል።

መጽሐፍቱ ባለመድረሳቸው የማስተማር ሥነ-ዘዴውን ከተማሪ ተኮር መምህር ተኮር አድርጎታል። ተማሪዎች ቀድመው አንብበው ጠያቂ እንዳይሆኑም አድርጓል። ይህም የትምህርት ጥራት ላይ የራሱን ጥላ ያጠላል ብለዋል።

ችግሩ እስኪቀረፍ ድረስ መምህራን በነባሩ የትምህርት ሥርዓትና መጽሐፍ ቢያስተምሩና ተማሪዎችም ቢማሩ የተሻለ ይሆን እንደነበርም መምህራኖቹ አመላክተዋል።

አሁን ያለው የመማር ማስተማር ሂደት ለተማሪዎች በተሰጣቸው ማስታወሻ ላይ ብቻ እንዲገደቡና የማንበብ ፍላጎታቻውና አቅማቸውን እንዳይዳብር ያደርጋል ብለዋል።

በሶፍት ኮፒ የመጣው ሞጁልም ከመማር ማስተማር መርሃ-ግበሩ ጋር የሚሔድ አይደለም ያሉት መምህራኑ፣ የምዕራፍ መዘበራረቅ ያለበትና የትምህርት እቅድ አዘገጃጀትን ለመጠበቅ የማይረዳ መሆኑን ገልጸዋል።

በሞጁል መልኩ የመጡ የተወሰኑ ምዕራፎች መምህራን በዓመቱ ዕቅድ መሰረት እንዳይራመዱ አድርጓቸዋል ሲሉም ተናግረዋል።

ስማቸው እንዳይጠቀስ የፈለጉት የምኒልክ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በበኩላቸው፤ የግል ትምህርት ቤቶችን ክፍያና የማጣቀሻ መጽሐፍትን ወጪ ስለማንችል በመንግሥት ትምህርት ቤት እየተማርን ነው፤ ይሁንና በትምህርት ቤታችን የካሪኩለሙ የትምህርት መጽሐፍት ተደራሽ ባለመሆናቸው ትምህርታችንን ፈታኝ አድርጎታል ብለዋል።

የጥቁር አንበሳ መሰናዶ ትምህርት ቤት ተማሪው ናትናኤል ዮናስ በበኩሉ እንደተናገረው፣ የአዲሱ ሥርዓተ-ትምህርት መጽሐፍት ታትመው እጃቸው አልገቡም። መጽሐፉ እጃችን ላይ ሳይደርስ የትምህርት ዘመኑ እየተጋመሰ ይገኛል። በመሆኑም በወቅቱ ማግኘት ያለብንን ዕውቀት ይገድባል ብሏል።

ተማሪ ናትናኤል አክሎም፣ በአገር አቀፍ ፈተና ውጤት የምንወዳደረው ከግል ትምህርት ቤቶች ጋር ጭምር ነው። በዚህ የተነሳ በውጤታችን ላይ ተጽዕኖው ይኖረዋል ሲል ስጋቱን ገልጿል።

የኮከበ ፅባህ መሰናዶ ትምህርት ቤት ተማሪ የሆነችው ሊዲያ ሀብታሙ በበኩሏ፣ በመፅሐፉ ሳንታገዝ የምንማረው የትምህርት ሂደት ውጤታማነታችን ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ስላለው አሁንም በተቻለ መጠን ሊታሰብበት ይገባል ስትል አስገንዝባለች።

ተማሪዋ አክላም፣ በአገር አቀፍ ፈተና ውጤት የምንወዳደረው ከግል ትምህርት ቤቶች ጋር በመሆኑ የመንግሥት ትምህርት ቤት ተማሪዎች ላይ ችግሩ እንካይከፋ ያሳስባል ስትል ተናግራለች።

የአዲስ አበባ ከተማ ትምህርት ቢሮ ከታህሳስ አንድ ቀን ጀምሮ በሁሉም ትምህርት ቤቶች መጽሃፍትን ለማዳረስ እየሰራ መሆኑን ገልጾ ነበር። ሆኖም ከቢሮው መረጃ ለማግኘት ያደረግነው ተደጋጋሚ ሙከራ ሊሳካልን አልቻለም።

# “ሰላም ከሰፈነ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ሁሉም ብሔር ብሔረሰቦች በመካከላቸው የሚፈጠሩትን ግጭቶች ተበዳይና ይቅርባይ ሆነው የሚፈቱበትና ፍትሕን የሚዳኙበት ባሕል አላቸው ያሉት አቶ አባተ፤ የተፈጠረውን ችግር ለመፍታት ተሸናፊ ፣ ተበዳይና ይቅር ባይ ሆኖ በመቅረብ በቀላሉ ግጭቶቹ የሚፈቱበት ሁኔታ በአገር ደረጃ ተግባራዊ ቢደረግ እልቂትና ውድመት ቦታ አይኖራቸውም ብለዋል።

እንደ አቶ አባተ ማብራሪያ፣ በኢትዮጵያ በይደር የመጡ ብዙ ጥያቄዎች አሉ። ለእነዚህ ጥያቄዎች በሂደት ካልሆነ በቀር በአንድ ጀምበር እልባት መስጠት አይቻልም። ነገር ግን ባለፉት አራት ዓመታት በጦርነትና በውስብስብ ችግር ውስጥ ሆኖ ጥያቄዎቹን በተወሰነ መልኩ ለመፍታት የተሔደው ርቀት እንደ ቀላል የሚታይ አይደለም። በደቡብ ክልል እየተነሳ ያለው የመዋቅር ጥያቄ በአግባቡ እየተመለሰ ነው፤ ቀሪው ሰላም ከሰፈነ እንደሚመለስ ጥርጥር የለኝም ብለዋል።

በተደጋጋሚ በአገሪቱ የሚከሰተውን ድርቅ ለመቋቋም በተለይም በአረንጓዴ አሻራ ፕሮግራም፣ በግብርናና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ፣ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ በተለይ በስንዴ ምርት እና አዲስ አበባ ከተማን ጨምሮ በቱሪዝም ዘርፍ የተሰሩ አስደማሚ ሥራዎችን ማድነቅና ለአገሪቱ መጻኢ እድል ተስፋ ሰጪ መሆናቸውን የገለፁት አቶ አባተ፤ የተከናወኑ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎችን ለሁሉም የህብረተሰብ ክፍል የማስጎብኘት ሥራ በስፋት መሰራት እንዳለበት ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ ባለፉት አራት ዓመታት ያውም በውስብስብ ችግሮች ውስጥ ሆና ያስመዘገበችው ኢኮኖሚያዊ እድገት ሊበረታታ የሚገባው ነው። የጸጥታ ችግሮች በሚገባ ከተፈቱ ኢትዮጵያ የዛሬ አስር ዓመት የእድገት ማማ ላይ የማትሆንበት ምክንያት እንደሌለም አቶ አባተ አስረድተዋል።



# ክፍት የሥራ መደብ ማስታወቂያ

**የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት ከዚህ በታች በተገለፁት ክፍት የሥራ መደቦች ላይ አመልካቾችን በቋሚነት አወዳድሮ የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ማዕከላት ሥር በሚገኙ ጣቢያዎች እና ኤርፖርቶች ላይ ማሰማራት ይፈልጋል።**

| ተ.ቁ | የሥራ መደብ መጠሪያ | ደረጃ | ደመወዝ | ብዛት | የትምህርት ደረጃ / ተፈላጊ ችሎታ | የሥራ ቦታ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የሚቲዎሮሎጂ ሳይንስ ጀማሪ ተመራማሪ | X | 5,352.00 ብር | 40 | በሚቲዎሮሎጂ ትምህርት መስክ የመጀመሪያ ዲግሪ ወይም በፊዚክስ ወይም በማቲማቲክስ ወይም በኬሚስትሪ ወይም በኮምፒዩተር ሳይንስ የመጀመሪ ዲግሪ 0 የሥራ ልምድ | |
| 2 | የሚቲዎሮሎጂ ሳይንስ ረዳት ተመራማሪ I | XII | 7,071.00 ብር | 3 | በሚቲዎሮሎጂ የትምህርት መስክ የመጀመሪያ ዲግሪ ወይም በፊዚክስ ወይም በሂሳብ ወይም በኬሚስትሪ ወይም በስታቲስቲክስ ወይም ኮምፒውተር ሳይንስ የትምህርት መስክ የመጀመሪያ ዲግሪ እና በዓለም የሚቲዎሮሎጂ ድርጅት Postgraduate ወይም ዓሚድ ሚቲዎሮሎጂካል ፎርካስቲንግ ዲፕሎማ የስራ ልምድ ቀጥታ አግባብነት ያለው 2 ዓመት | |
| 3 | የሚቲዎሮሎጂ ሳይንስ ረዳት ተመራማሪ II | XIV | 9,056.00 ብር | 4 | በሚቲዎሮሎጂ የትምህርት መስክ የመጀመሪያ ዲግሪ ወይም በፊዚክስ ወይም በሂሳብ ወይም በኬሚስትሪ ወይም በስታቲስቲክስ ወይም ኮምፒውተር ሳይንስ የትምህርት መስክ የመጀመሪያ ዲግሪ እና በዓለም የሚቲዎሮሎጂ ድርጅት Postgraduate ወይም ዓሚድ ሚቲዎሮሎጂካል ፎርካስቲንግ ዲፕሎማ የስራ ልምድ ቀጥታ አግባብነት ያለው 4 ዓመት | |
| 4 | የዕቃ ግምጃ ቤት ኃላፊ I | X | 5,352.00 ብር | 1 | ኮሌጅ ዲፕሎማ ወይም የቴክኒክና ሙያ በደረጃ 3 /10+3/ COC ምዘና ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሰፕላይስ ማኔጅመንት፣ ፕሮርክዩርመንትና ሰፕላይ ማኔጅመንት፣ ቢዝነስ ማኔጅመንት፣ ሴልስ ማንሺፕ፣ ሴልስ ማኔጅመንት፣ ማርኬቲንግ፣ ማርኬቲንግ ማኔጅመንት፣ ሎጅስቲክና ሰፕላይ ቼን ማኔጅመንት፣ ሎጀስቲክስ፤ ማቴሪያል ማኔጅመንት፤ ፐርቼዚንግ ማኔጅመንት ማኔጅመንት፤ ሎጂስቲክስና ሰፕላይ ማኔጅመንት፣ ፕሮፐርቲ አድሚኒስትሬሽን፣ ፐርቼዚንግ እና ሰፕላይ ማኔጅመንት ሴልስና ሰፕላይ ማኔጅመንት፣ ኮኦፐሬትቭ ቢዝነስ ማኔጅመንት፣ ሎጅስቲክስ እና ፕሮክዩርመንት፣ ማርኬቲንግና ሰፕላይ ማኔጅመንት እና ቀጥታ አግባብ ያለው 5 ዓመት የስራ ልምድ | አዳማ |
| 5 | ዋና ገንዘብ ያዥ | VIII | 3,934,00 ብር | 1 | ኮሌጅ ዲፕሎማ ወይም የቴክኒክና ሙያ በደረጃ 3 /10+3/ COC ምዘና ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በሂሳብና መዝገብ አያያዝ፣ እና ቀጥታ አግባብ ያለው 2 ዓመት የስራ ልምድ | አዳማ |

በሥራ መደቡ ላይ ማመልከት የምትፈልጉ አመልከቾች የትምህርትና የሥራ ልምድ ማስረጃችሁን ዋና እና የማይመለስ ኮፒ እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎች በመያዝ ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ዘመን ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ሰባት/7/ ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ በግንባር ወይም በወኪል መመዝገብ የምትችሉ መሆኑን እናሳውቃለን።

**የመመዝገቢያ ቦታ፤**

- ጥቁር አንበሳ አጠገብ በሚገኘው የኢንስቲትቱ ዋና መ/ቤት ቢሮ ቁጥር 106፤- አዲስ አበባ
- ለአማራ ክልል የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ማዕከል- ባህርዳር እና ኮምቦልቻ
- ለኦሮሚያ ክልል የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ማዕከላት - አዳማ፣ ጅማ እና ባሌ ሮቤ
- ለደ/ብ/ብ/ህ ክልል የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ማዕከል፣ ሀዋሳ
- ለጋምቤላ ክልል የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ማዕከል፣ ጋምቤላ
- ለሱማሌ፣አጎራባች ክልል የሜቲዎሮሎጂ አገልግሎት ማዕከል -ጅጅጋ
- ለቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ማዕከል -አሶሳ
- ለአፋር ክልል ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ማዕከል - ሠመራ

**ማሳሰቢያ፡-**

- የሥራ ቦታ፡ - በክልል ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ማዕከላት ።
- ለተጨማሪ መረጃ፡ -

**በስልክ ቁጥር +251-11-515-8708 ወይም +251-11-551 22 99 ፣**

**ፖሣ.ቁ. 1090**

**የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት**
**አዲስ አበባ**

# ስፖርት





## «ጌታነህ ከበደ ዘግይቶ በመምጣቱ አሰናብቼዋለሁ»

-አሰልጣኝ ውበቱ አባተ

ብርሃን ፈይሳ




ከሳምንት በኋላ በአልጄሪያ አዘጋጅነት በሚካሄደው ሰባተኛው የአፍሪካ አገራት ቻምፒየን ሺፕ(ቻን) ውድድር ላይ የሚሳተፈው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ከቀናት በፊት ዝግጅት መጀመሩ ይታወቃል። የብሔራዊ ቡድኑ ዋና አሰልጣኝ ውበቱ አባተ ኢትዮጵያ በውድድሩ ለሶስተኛ ጊዜ ስትሳተፍ የተሻለ ውጤት የማስመዝገብ ሃላፊነት የተጣለባቸው ሲሆን ለሃያ ስምንት ተጫዋቾች ጥሪ በማድረግ ወደ ዝግጅት ገብተዋል። ይሁን እንጂ ቡድኑ ዝግጅቱን ሲጀምር ወሳኙ የአጥቂ ስፍራ ተጫዋች ጌታነህ ከበደ ጥሪ ከተደረገላቸው ተጫዋቾች መካከል መገኘት እንዳልቻለ ታውቋል። ከትናንት በስቲያ ሶከር ኢትዮጵያ ባስነበበው ዘገባ መሰረት የቡድኑ ቁልፍ የፊት መስመር ተጫዋች ጌታነህ ከበደ ራሱን ከብሔራዊ ቡድኑ ማግለሉ ተጠቁሟል።

ጌታነህ ከበደ ወደ ብሔራዊ ቡድኑ እንዲመለስ በኢትዮጵያ እግር ኳስ አመራሮች ከፍተኛ የማግባባት ስራ ሲሰራ እንደነበረ ዘገባው የጠቆመ ሲሆን ተጫዋቹ እዚህ ውሳኔ ላይ የደረሰው አስቦበት መሆኑን አሳውቋል።

ከ2001 ጀምሮ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ወሳኝ አጥቂ በመሆን ያገለገለው ጌታነህ በሀገሩ መለያ 33 ግቦችን በማስቆጠር ትልቅ ታሪክ መስራቱ ይታወቃል። ጌታነህ አሰልጣኝ ውበቱ የዋልያዎቹ መሪ ሆነውም ቡድኑን በአምበልነት ማገልገል የቻለ ሲሆን ካለፈው ግንቦት ወር ጀምሮ በአሰልጣኙና ተጫዋቹ መካከል አለመግባባት መፈጠሩ ይታወሳል። በሁለቱ ግለሰቦች መካከል አለመግባባት የተፈጠረው በአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ ዋልያዎቹ ማላዊና ግብጽን በገጠሙባቸው ጨዋታዎች ጌታነህ በፕሪሚየር ሊጉ ከፍተኛ ግብ አስቆጣሪ በነበረበት ሰዓት አሰልጣኝ ውበቱ ተጫዋቹን ከቡድኑ በመቀነሳቸው ነበር። ለዚህም አሰልጣኙ "ደጋግሜ ስልክ ስደውልለት አለማንሳቱ የዲሲፕሊን ችግር በመሆኑ ከቡድኑ ውጭ አድርጌዋለሁ" የሚል ምላሽ የሰጡ ሲሆን ጌታነህ በበኩሉ "የዲሲፕሊን ችግር የለብኝም ስልኩን ለምን እንዳላነሳሁ ግን አሰልጣኝ ውበቱ በደንብ ያውቃል" ሲል በወቅቱ አስተባብሎ ነበር።

አሰልጣኝ ውበቱ ከጌታነህ ጋር አለመግባባቱ በተፈጠረበት ወቅት ከተጫዋቹ ጋር ሌላ ችግር እንደሌለባቸውና ብቃቱ ጥሩ እስከሆነ ድረስ ዳግም ለብሔራዊ ቡድኑ ሊጠሩት እንደሚችሉ ጠቁመው ነበር። በዚህም መሰረት ከስምንት ወር በኋላ ለተጫዋቹ ጥሪ አቅርበዋል። ይሁን እንጂ ጌታነህ ብሔራዊ ቡድኑ ወሳኝ አህጉራዊ ውድድር ሊያደርግ ጥቂት ቀናት በቀሩበት በዚህ ወቅት ያልተጠበቀ ውሳኔ ወስኗል። ይህም በስፖርት ቤተሰቡ ዘንድ ተጫዋቹ ራሱን በዚህ ሰዓት ከብሔራዊ ቡድኑ ያገለለው ባለፈው ቁርሾ ይሆናል የሚል ጥርጣሬ ማሳደሩ አልቀረም።

አሰልጣኝ ውበቱ ትናንት የቡድኑን የቻን ዝግጅት በተመለከተ መግለጫ በሰጡበት መድረክ በጌታነህ ከበደ ጉዳይ ለተነሳው ጥያቄ ምላሽ ሲሰጡ፣ ተጫዋቾች ወደ ብሔራዊ ቡድን እንዲገቡ ጥሪ በቀረበላቸው ቀን መሰረት ጌታነህ ቀኑን አክብሮ ባለመገኘቱና ዘግይቶ በመምጣቱ እንደተቀነሰ አብራርተዋል፡፡

«የጥሪ ቀን ባለማክበሩና በመዘግየቱ ጌታነህ ከበደን ለምን ዘገየህ ስለው ጥሪውን ስላልሰማሁ ነው አለ፣ እንዴት አይሰማም? እሱን ብቀበል በጊዜ አልመጡም ብዬ ያሰናበትኳቸውን እንዴት እመራለሁ፣ ስለዚህ ከቡድኑ አሰናብቼዋለሁ» ያሉት አሰልጣኝ ውበቱ ጌታነህ «ራሴን ከቡድኑ አግልያለሁ» ማለቱንም ከሚዲያ መስማታቸውን ተናግረዋል፡፡

ተጫዋቾች ባለፈው ታኅሣሥ 18/2015 ቀርበው ሪፖርት እንዲያደርጉ ጥሪ መቅረቡን ያስታወሱት አሰልጣኙ፣ ጌታነህ ከበደ ብቻ ሳይሆን በተጠቀሰው ቀን ያልተገኙ ሌሎች ተጫዋቾች ከቡድኑ መቀነሳቸው ገልፀዋል፡፡ ከነዚህ መካከል ታፈሰ ሰለሞንና አማኑዔል ገብረሚካኤል የሚገኙ ሲሆን ጌታነህ ከተጠቀሰው አንድ ቀን ዘግይቶ ቢገኝም ሪፖርት እንዳላደረገ አስረድተዋል፡፡ በመሆኑም እንዲህ አይነት ተጫዋች ከቡድናቸው ጋር ለማስቀጠል እንደሚቸገሩ ጠቁመው ተጫዋቾች ለብሔራዊ ቡድን ክብር ሊኖራቸው እንደሚገባና ህግም መከበር እንዳለበት ተናግረዋል፡፡

« እንዴት በሊጉ 29 ግብ ያስቆጠረው አቡበከር ናስር እያለ ጌታነህ ከበደ በቋሚነት ይጫወታል የሚል በርካታ ወቀሳ እየደረሰብኝ ሳጫውተውም ነበር፣ በዕርግጥ አቅምም ስለነበረው ነው፣ በተያያዘም እንዴት ከቅዱስ ጊዮርጊስ ጋር ጥሩ ባልነበረ መልኩ የተለያየውን እና ጉዳት ላይ የነበረውን ተጫዋች ይመርጣል ተብዬ ብዙ ስታማ በነበረበት ወቅት ጫናዎችን ተቋቁሜ ተጫዋቹን ስመርጥ እና ሳጫውት ነበር። በመጨረሻም ጌታነህ ከብሔራዊ ቡድኑ ማግለሉን ሰማሁ ውሳኔው የራሱ ነው። ምናልባት ስሜታዊ ሆኖ ሊሆን ይችላል ነገር ግን ውሳኔውን አከብራለሁ» በማለትም አሰልጣኝ ውበቱ ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡

## አማራ ክልል

ለአቶ ሙንየ ሀብቴ ባሉበት ይግባኝ ባይ፡-የአብክመ ፍትህ ቢሮ ዐ/ሕግ መልስ ሰጭ፡-............... ሙንየ ሀብቴ መካከል ስላለው ከባድ ሰው መግደል ወንጀል ክስ ይግባኝ ጉዳይ መልስ ሰጭ በተደጋጋሚ ቢታዘዝም ያልቀረቡ ስለሆነ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግልወት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡በመሆኑም መልስ ሰጭ አብክመ ጠቅላይ ፍ/ቤት /የተከሰሱ/ይግባኝ ክርክር የቀረበብዎት መሆኑን አውቀው ለጥር 22 ቀን 2015 ዓ/ም ከጠዋቱ 2፡30 ለሆነው ቀጠሮ አማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ደብረ ማርቆስ ከተማ ተዘዋዋሪ ወንጀል ችሎት እንዲቀርቡ በዚህ የጥሪ ማስታወቂያ መሠረት የማይቀርቡ ከሆነ ግን ጉዳዩ በሌሉበት ታይቶ ተገቢውን ውሳኔ የሚወሰን መሆኑን እንዲያውቁት ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት**
**የደብረ ማርቆስ ተዘዋዋሪ ችሎት**

የባለንብረቱ ስም ተስፋዬ ፈለቀ የሰሌዳ ቁጥር 3-3163 የሻንሲ ቁጥር MD2A18AZOHWL27210 የሞተር ቁጥር DUZWHL44960 የተሽከርካሪው ዓይነት ሞተር ሳይክል ሞዴል Boxer-5 ከላይ ደረጃው የተገለፀው የተሽከርካሪ ሠሌዳ ስለጠፋብኝ ብለው በ29/3/2015 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሰርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍርድ ቤት ማስረጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያሳወቅን ይህ ባይሆን ግን ለአመልካቹ ተለዋጭ ሰሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በባር ዳር ከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ጽ/ቤት**

## አዲስ አበባ አስተዳደር

የባለንብረት ስም ፓንአፍሪካ ግሎባል ኃላ/የተ/የግ/ማ የሰሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-12225 የተሽከርካሪው አይነት ተሳቢ የሻንሲ ቁጥር LC99383L977ZKS800 ሞዴል KS93S82LB የሞተር ቁጥር Trailer የሊብሬ ቁጥር 0052122/0089636 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 12/4/2015 አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የኮልፌ ቀራኒዮ ቅ/ጽ/ቤት**

ከሣሽ ልዩ የገንዘብና እገዛ ተቋም አ.ማ
ተከሣሽ እነ አለምነሽ ተሾመ መኮንን
ማሪቱ ፈንታ ፈረደ
መካከል ፍ/ብሔር ስላለው ክስ ጉዳይ ተከሣሽ በ01/05/2015 ዓ.ም. ለሆነው ቀጠሮ በ4፡00 ሰዓት ለመ/ደ/ፍ/ቤት የካ ምድብ 4ኛ ፍ/ብሔር ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት**

የባለንብረት ስም ብሩክ ልጁ ሰባኔ የሰሌዳ ቁጥር አአ 01-01-01560 የተሽከርካሪው አይነት አነስተኛ አውቶቡስ (ከ12 ያነሰ መቀመጫ) የሻንሲ ቁጥር JT1VY-H61V00023786 ሞዴል YH61LV-JRBFW የሞተር ቁጥር 3y-0216449 የሊብሬ ቁጥር 069836 ከላይ መረጃቸው የተገለፀው የተሽከርካሪ ባለንብረት የፊት ሰሌዳ የጠፋባቸው ለመሆኑ ከአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ፖሊስ ጣቢያ በደብዳቤ ቁጥር 10778/15 ለመጥፋቱ ማስረጃ ያቀረቡ በመሆኑ ሰሌዳው በእናንተ በኩል ተሠርቶ እንዲሰጣቸው እንጠይቃለን የፖሊስ ማስረጃና የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር ፎቶ ኮፒ አባሪ አድርገን የላክን መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የአቃቂ ቃሊቲ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ሰርካዲስ ተስፋዬ መኮንን የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-76383 የተሽከርካሪው አይነት አውቶሞቢል የሻንሲ ቁጥር LLV2A3A26B0220155 ሞዴል LF7162E የሞተር ቁጥር LF48103*110601323 የሊብሬ ቁጥር 136070 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 12/4/2015 አመልክተዋል፡ ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የአዲስ ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም አማረ ጌትነት ዳምጤ የሰሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-87323 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻንሲ ቁጥር LZZ 5BlSF7GN131250 ሞዴል ZZ1257S4341W የሞተር ቁጥር WD615.47* 160617011217* የሊብሬ ቁጥር 0073694/0291486 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 13/4/2015 አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የአዲስ ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

አመልካች/ከሳሽ ወ/ሮ ብርቱካን አዋሽ ተጠሪ/ተከሳሽ አቶ ተስፋዬ አበበ ስላለው የፍ/ብሄር ክርክር ጉዳይ ተጠሪ/ተከሳሽ አቶ ተስፋዬ አበበ በ1/5/2015 ዓ.ም በ4፡30 ሰዓት በሬጅስትራር መልስ በፅሁፍ እንዲያቀርቡ እንዲሁም በ2/5/2015 ዓ.ም በ4፡30 ሰዓት በችሎት ለክስ መስማት እንዲቀርቡ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት አዲስ ከተማ ምድብ 1ኛ ቤተሰብ ፍ/ብሔር ችሎት አዟል፡፡
የከሳሽ/አመልካች ክስ ከሬጅስትራር ፅ/ቤት ከቀጠሮ ቀን በፊት ቀርበው እንዲወስዱ እናሳስባለን፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት**

የባለንብረት ስም ብርሃኑ አስፋው ወልደየስ የሰሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-46075 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻንሲ ቁጥር WJME3TRS40C231891 ሞዴል AT380T38H የሞተር ቁጥር F3BEE681 G*B201-160198*የሊብሬ ቁጥር 003129/0132856 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 11/4/2015 አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የልደታ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም በረከት ጌታቸው ካህሳይ የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-B47653 የተሽከርካሪው አይነት አውቶሞቢል የሻንሲ ቁጥር LLV2A2A11A0061688 ሞዴል LF520 የሞተር ቁጥር LF479Q3* 101100092* የሊብሬ ቁጥር 391731/391735 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 13/4/2015 አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የቦሌ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ሊያ ገ/የሱስ ተ/ፅዮን የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-B47451 የተሽከርካሪው አይነት አውቶሞቢል የሻንሲ ቁጥር L6T7524S0EN027363 ሞዴል CK08 የሞተር ቁጥር MR479Q*E5N297849* የሊብሬ ቁጥር 424912 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 12/4/2015 አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የካ ቅ/ጽ/ቤት**

በይግባኝ ባይ -ዩክሮ አግሮ ኢንዱስትሪ ኃ/ተ/የግ/ማ በመልስ ሰጪ-እነ የኦሮሚያ ኢንቨስት መንት እና ኢንዱስትሪ ቢሮ መካከል ባለው የፍትሐብሔር ክርክር ጉዳይ 2ኛ መልስ ሰጪ አቶ ተይሲር አባጆብር ለጥር 15 ቀን 2015 ዓ.ም ለሆነው ቀጠሮ ከጠዋቱ 3:30 ሰዓት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት 1ኛ ፍትሐብሔር ይግባኝ ሰሚ ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት**